ምዕራፍ ሁለት

የመሪ ኃላፊነት፥ ሥልጣንና ተጠያቂነት

«የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ተሰጠኝ መጠን እንደ ብልሃተኛ የአናጺ አለቃ መሠረትን መሠረትሁ፥ ሌላውም በላዩ ያንጽል። እያንዳንዱ ግን በእርሱ ላይ እንዴት እንዲያንጽ ይጠንቀቅ።» (1ኛ ቆሮንቶስ 3፥10ን ይመልከቱ)። በምዕራፍ 9፥19 እንደሚለው ደግሞ፥ *«ከሰው ሁሉ አርነት የወጣሁ ሰሆን የሚበልጡትን እንድጠቅም እንደ ባሪያ ራሴን ለሁሉ አስገዛለሁ።»* ይህንን የሚለው ጳውሎስ ነበር። አይሁዳዊ ሆኖ ራሱን ባሪያ ነኝ ማለት ከባድ ነው። በመሠረቱ መሪነት የኃላፊነት ቀንበር መሸከም ነው። ቀጥለን የመሪን የተግባር ኃላፊነት፥ ሥልጣንና ተጠያቂነት በዝርዝር እንመለከታለን።

2.1. የመሪ ኃላፊነት

ኃላፊነት *(Responsibility)* ባላደራ መሆንንና ተጠያቂነትን በማሰብ የሚከናወን የተግባር ባለቤትነትን መረከብ ሊሆን ይችላል። ኃላፊነት የተለያየ ደረጃና ድርሻ ወይም የክልል ገደብ ቢኖረውም ተጠያቂነትን *(Accountability)* አያስቀርም። ሕግ ከሌለ በስተቀር ማንም ከሕግ በላይ ሊሆን አይችልምና።

እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ወንጌልን የማዳረስ ኃላፊነት ሰጥቷታል። በመሆኑም ወንጌልን ማዳረስ ተቀዳሚ ተግባሯ ሆኖ በአግባቡ ለማዳረስ ግን ነገሮችን ማመቻቸት የውዴታ ግዴታዋ ነው። ይህም ለሰዎች ሁሉ የተሰጠ ኃላፊነት ሲሆን በተለይ የታላቁን ተልእኮ ትእዛዝት መተግበር ይጠበቅባታል። በዚህም ለመሪዎች የተሰጣቸው ኃላፊነት በቀላሉ የሚገመት አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል። መሪዎች ሕዝብን ሊያጠፉም ሊያለሙም የሚችሉ ናቸው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኃላፊነቱን የዘነጋ መሪ ቢኖር አሮን ነበር። በፍርሃትና በምንቸገረኝነት ሕዝቡን ስድ ለቅቆ ለጣዖት አምልኮ የዳረጋቸው የተሰጠውን አደራ ባለመወጣቱ ነበር።

በማንኛውም ደረጃ ያሉ መሪዎች ራሳቸውን ሳይገሥጹና ሳይመክሩ ሕዝቡን ሊገስጹ አይችሉም። ራሳቸውን ሳያስተካክሉና ሳያጸዱ ሕዝቡን ሊያጸዱና ሊያስተካክሉ አይችሉም።

አንድ ጊዜ ንጉሥ ሳኦል ኃጢአተኞቹን አማሌቃውያን እንዲያጠፋ በነቢይ በኩል የእግዚአብሔር መመሪያ ተሰጥቶት ነበር። እርሱም ያደረገውን አደረገና ሌሎችን አተረፈ። ለምርኮ ሳሰቶ ሕዝቡንም ደስ ያሰኙትን ሁሉ አዳናቸው። የተሰጠው ትእዛዝ ግን ሁሉን ማጥፋት ስለነበር፥ ያን ባለማድረጉ ሥልጣነ መንግሥቱ ከእርሱ እንደተቀደደች በ1ኛ ሳሙኤል 15 ውስጥ እናነባለን። በተለይ ቁጥር 24 ውስጥ፥ *«ሕዝቡን ስለፈራሁ ቃላቸውንም ስለሰማሁ፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝና የአንተን ቃል [የሳሙኤልን] በመተላለፍ በድያለሁ»* ሲል ኃላፊነቱን አለመወጣቱን በፍርሃት መለወጡን በደንብ አምኗል። ግን ጊዜው በጣም ዘግይቷል። ሕዝቡን ከሚፈራ እግዚአብሔርን ቢፈራ ይሻለው ነበር። አሮንም ይህንኑ ነበር ያደረገው። በዚህም ሳኦል መንግሥቱ ተቀደደች። ለሌላ ያውም ለጦር አዝማቹ ለዳዊት ተሰጠች።

ኃላፊነት ጥንቃቄን ይጠይቃል፤ ካልሆነ አለመቀበል ይበጃል። እግዚአብሔር የሕዝቡን ጩኸት ይሰማል። ጽዋ ሲሞላም በጊዜው ለፍርድ ይነሣል። ጥንትም እንዳደረገ አሁንም ሊያደርግ ቢፈልግ ማን ከልክሎት?

በዚህ አጋጣሚ ይህችን መጽሐፍ ለሚያነቡ ሁሉ ለማስገንዘብ የምወደው በምንም ደረጃ ቢሆን የተሰጠ ኃላፊነት ተጠያቂነትን የሚያስቀር ባለመሆኑ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ መሆኑን ነው። ኃላፊነትን ተቀብሎ ከማዝረክረክ አለመቀበል ይሻላል። ምናለ ዕድሉና ጊዜው ላላቸው ለሌሎች ቢሰጥ? ለታይታና ለስም መጠሪያ ብቻ የተደረገ ኃላፊነት እጅግ በደል ነው። በመንፈሳዊ መስክም ሆነ በሌላ የተሰማሩ ይህ ይመለከታቸዋል። አካል ሁሉ ድርሻ ስለሚኖረው ለዕድገት እንዲበቃ መንቀሳቀስ ይኖርበታል።

በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የመሪዎች ኃላፊነት በአሁኑ ወቅት ትኩረት የሚሻ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል። ስለሆነም መሪዎች የእግዚአብሔርን ቤት በሥርዓት ማስተዳደር ይጠበቅባቸዋል። መሪዎችን በሚመለከት ጳውሎስ እንደጠቀሰው መሪ፡-

ሀ. ገንዘብን የማይወድ፡-

በ (1ኛ ጢሞቴዎስ 3፥4 ይመልከቱ)። በሌላ ስፍራ *«ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፥ አንዳንዶችም ይህን ሲመኙ፥*

ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ» ይላል። (1ኛ ጢሞቴዎስ 6፥10ን ይመልከቱ)። በእርግጥ ገንዘብ ጥሩ ባሪያ ሲሆን ክፉ ጌታ ግን ነው። የብዙ ሰዎች፥ እንዲያውም የብዙ መሪዎች የቅሌት ምንጭ ገንዘብ ለመሆኑ እምብዛም እማኝ የሚያስጠይቅ አይመስለኝም። ለመሳት ወይም ለማሳት፥ ለመሾም ወይ ለመሻር፥ ለመጥቀም ወይም ሌላውን ለመጉዳት የገንዘብ ሚና ከፍተኛ እየሆነ መጥቷል። ቤተ ክርስቲያንንም እየተፈታተናት ያለ ክፉ ባላጋራ ይመስለኛል።

ከጥቅም ጋር የተያያዘ ነገር ሁሉ ከደም ሥራችን ጋር እንደተያያዘ ነገር ሲጎዳን ይታያል። ይህ ሁሉ መሯሯጥና ትርምስ፥ ውጊያና ጦርነት፥ ፍርሃትና ሽብር ወዘተ... ከግል ሁኔታ ጋር የተያያዘ ሊሆንም ይችላል። እጁን ከዚህ የሚሰበስብ፥ ራሱን ለገንዘብ ባሪያ የማያደርግ መሪ ምንኛ የታደለ ይሆን? አንዳንዴ ሲሰበስብ ከርሞ ሳይጣላው በድንገት ይሞታል? አንድ ጊዜ ታዋቂው አሜሪካዊ ከበርቴ ሮክ ፌለር፥ «ገንዘብ በቃኝ የሚባለው መቼ ነው?» ሲሉት «ትንሽ ሲጨመር» ነው ብሏል። መሪ እንደዚህ ዓይነት ፈተና ሲመጣበት ቶሎ መፍትሔ ቢፈልግ ይሻላል። እንደ ተጻፈ፥ «አንተ ግን፥ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከዚህ ሽሽ» (1ኛ ጢሞቴዎስ 6፥11ን ይመልከቱ)።

ለ. ቤተሰቡን በሥርዓት የሚያስተዳድር፦

«ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፤ ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ፥ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃል?» (1ኛ ጢሞቴዎስ 3፥4-5ን ይመልከቱ)። ይህም ችላ ሊባል የሚገባው ጉዳይ አይደለም። ምክንያቱም የትውልድ ሥርዓት ብልሹነት የሚጀምረው ከቤት በመሆኑ። አባቱ ታማኝ ሆኖ ያላየ ልጅ በምን ተአምር ታማኝ ይሆናል? ስለዚህ አባቶችና እናቶች ድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል።

ሐ. ምሳሌያዊ የሚሆን፦

በ1ኛ ጴጥሮስ 5፥3 ውስጥ እንደተጠቀሰው፥ «ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ» ተብሏል። የሚያወራ ብቻ እንጂ የማይሠራ/ተግባራዊ ያልሆነ መሪ ምሳሌያዊ *(Exemplary)* ሊሆን ፈጽሞ አይችልም። በተበተነው መጠይቅ ውስጥ የዘመኑ መሪዎች ባሕርይ ምን ይመስልዎታል? የሚለውን

ጥያቄ *[38.1%]* የሚሆኑ ሰዎች በአፍ የሚያወሩ ብቻ ናቸው በማለት መልሰዋል።

መ. መንጋውን መጠበቅ የሚችልና ሽክም ያለው፡–

«–––በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፥ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጎብኙት።» (1ኛ ጴጥሮስ 5፥2) ሲል፥ የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊም በምዕራፍ 20፥28 ውስጥ «––የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ –––ተጠንቀቁ» ብሏል። ለመንጋው ግድ የሌለው መሪ ሞያተኛ እንጂ መሪ አይባልም። ሀገራቸው በረሃብ ስትደቆስ በስዊስ ባንክ ገንዘብ የሚያስቀምጡ የአፍሪካ መሪዎች የዚህ ምሳሌ ተጠቃሾች ናቸው። ለመንጋው ግድ የሌለውና ሕዝቡን ዘወር ብሎ የማይመለከት፥ እስኪመረጥ ብቻ ምሎ የሚገዘት መሪ ከአታላይ፥ ሲከፋም ከነፍሰ ገዳይ ተነጥሎ አይታይም።

ሠ. እውነትን የሚያስተምርና የሚገሥጽ፡–

ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 3፥2 ውስጥ እንደ ጠቀሰው መሪ መሆን የሚፈልግ ሰው፥ «–––ልከኛ፥ ራሱን የሚገዛ፥ እንደሚገባው የሚሠራ፥–––ለማስተማርም የሚበቃ» መሆን እንደሚገባው ይናገራል። ከዚህ በተረፈ፥ *«ሕይወት በሚገኝበት ትምህርት ደግሞ ሊመክር ተቃዋሚዎችንም ሊወቅስ ይችል ዘንድ፥ እንደ ተማረው በታመነ ቃል ይጽና። የማይታዘዙና ከንቱ የሚናገሩ የሚያታልሉም ይልቁንም ከተገረዙት ወገን የሚሆኑ ብዙ ናቸውና።»* (ቲቶ 1፥9–10ን ይመልከቱ)። ለዚህ እንደነዚህ ያሉ አስመሳዮችን አፋቸውን መዝጋት እንደሚገባ ቃሉ ራሱ ይናገራል። በዚያን ዘመን የተገረዙት ወገን ብዙ ይጠበቅባቸው ነበር። በእኛም ዘመን የተገረዙትን የሚወክሉት አማኞች መስመር ሲለቁ በዝምታ ማለፍ ለባሰ ችግር እንዲጋለጡ መፈለግን ያመለክታል። ሰው ሲስት ችላ ማለት፥ «የራሱ ጉዳይ! እኔ ምን ቸገረኝ» እንደ ማለት ነው።

ሥልጣን (Power/Authority) ማለት ኃላፊነቶችን የመጠቀምና የመተግበር መብት ሲሆን፥ ብይን የመስጠትን፥ የማዘዝንና የመሥራትን፥ የመግዛትንና የበላይነትን የሚያጎናጽፍ መብት ነው። አንዳንዱ የሥልጣን መብት ግን የማይገሠስና የማይደፈር ሆኖ እንደ መሪው ባሕርይ ፈርዖናዊ ፍጹምነትን ሲጠብቅ፥ ውድቀቱም እንደዚያው ፍጹም ይሆናል። ስለሆነም ገደብ የሌለው ሥልጣን፥ ገደብ የሌለው ወንጀል፥ በደልና ዝቅጠት እንዲሁም መበላሸት ያስከትላል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው» ይላል። (ሮሜ 13፥1-2፥ ዮሐንስ 19፥11 ይመልከቱ)። ባለሥልጣናት ከእግዚአብሔር ተሾመዋልና ሁሉ ሊታዘዛቸው ይገባል፤ ሆኖም የባለሥልጣኑ ትእዛዝ ሕግን አስካከበረና በመንፈሳዊም አመለካከት ከእግዚአብሔር ትእዛዛት ጋር ሲስማማ ብቻ ነው። ሐዋርያትም ያደረጉት ይህንኑ ነበር። (የሐዋርያት ሥራ 4፥19) ያነጻጽሩ።

እግዚአብሔር ሥልጣን ሲሰጥ ሕዝቡን እንዲመሩ፥ እንዲያስተዳድሩ፥ መንገድ እንዲያሳዩና ሥርዓት እንዲሰፍን ነው። ሕዝቡም ደግሞ ለመኳንንቱ የተሰጣቸው ሥልጣን ፍጹም ባለመሆኑ እንዲጸልዩላቸው አዟል። (1ኛ ጢሞ 2፥2ን ይመልከቱ)። ይህ ሳይሆን ሲቀር ግፍና በደል፥ ጉስቁልናና መራቆት፥ ሥርዓት አልበኝነትና እልቂት በምድር ላይ ይሆናል።

ባለሥልጣናት ሁልጊዜ ከእነርሱ በላይ ሌላ ባለሥልጣን እንዳለ መርሳት የለባቸውም። ማንም ከሕግ በላይ ሊሆን አይገባም፤ አይችልምም። *«ከፍ ካለው በላይ ከፍ ያለ ይመለከታልና፥ ከእነርሱም በላይ ደግሞ ሌሎች ከፍ ይላሉና»* እንዳለው ንጉሡ ሰሎሞን (በመክብብ 5፥8) የሚያደርጉትን ሁሉ በጥንቃቄ ቢያደርጉ ምንኛ በታደሉ ነበር። ዳሩ ግን የሥልጣን ወንበር የነበርንበትን አሰረስቶ ያባልጋልና በየደረጃው ያሉ መሪዎች የበላይ እንዳላቸው ይረሳሉ። የሥልጣን ካባ ሲሰጥ ዳግም የማይወሰድና የማይወልቅ ይመስላል። የማንም ቢሆን እግዚአብሔር ሲያወልቀው ይወልቃል።

አንድ ዘመን አንድ የማውቀው ም/የመቶ አለቃ የሆነ ሰው በደርግ መንግሥት የፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ኃላፊነት ደረጃ ሥልጣን ነበረው። አመጣጡ ከዝቅተኛ ቤተሰብ ያውም ከጉልት ሠፈር ወይም በዚያን ዘመን ቋንቋ የጆርባ አጥንቱ ከጭቁን መደብ ስለነበር፥ ሥልጣኑ እጅግ

አስክሮት የሚያደርገውን አጥቶ ነበር። መኪናም በግሉ እንደ አሁኖቹ ኮብራ መሰል ተሰጠው። ታዲያ አንድ ቀን የአንድ ድርጅት የሥራ መሪዎች፥ የመምሪያና የክፍል ኃላፊዎች፥ መኮንኖችና ባለ ሌላ ማዕረግ ወታደሮችም በተሰበሰቡበት የውይይት ክበብና መግለጫ ሊሰጥ ተጋብዘን ነበር። በጉባኤውም መካከል አያሌ ትልልቅ ሰዎች በዕድሜና በሥልጣን ይገኙ ነበር። ልከ እንደመጣም፥ «እንደምን ዋላችሁ ጓዶች?» አለ። ታዳሚውም በአፀፋው ባህል ነውና፥ «እግዚአብሔር ይመስገን» ብሎ መለሰ። መልኩ ልውጥውጥ አለና እንደገና ድምጹን ከፍ አድርጎ፥ «እንደምን ዋላችሁ ጓዶች!» አለ። አሁንም ድምጻችን ከፍ አለ እንጂ መልሱ ያው ሆነበት። ለሦስተኛ ጊዜ ደገመ። ሕዝቡ አልገባውምና ወይ ፍንክች መልሱ ያው ነበር። በጣም ተበሳጨና፥ «አይባልም ጓዶች፥ እናሸንፋለን! ነው የሚባለው» አለንና አረፈው። ለመጨረሻ ጊዜ ፈታኝ የሆነ ሰላምታ ሆኖ፥ «እንደ ምን ዋላችሁ ጓዶች?» ብሎ አቀረበ። ትእዛዝ መቀበላችንን ለማወቅ ይመስላል። እድምተኛውም ደነገጠ፥ ፍርሃት ተደበላልቆበት «እናሸንፋለን!» ብሎ ጮክ ባለ ድምጽ መለሰ። የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊም በጉባኤው መካከል ነበር። ይህም በሕይወቱ እስካሁን የማይረሳው ገጠመኝ ሆኖ ቀርቷል።

ጊዜው ሀገራችን በስተ ምሥራቅ በሶማሊያ መንግሥት ወረራ ላይ የነበረችበትና የቀይ ሽብርና የነጭ ሽብር ከፍተኛ የፍልሚያ ወቅት ነበር። የትዕቢት ማሸነፍ መሸነፍ መሆኑን ያልተረዳው ያ ሰው፥ ይህንን ባለን አንድ ወር ገደማ ለቀበሌ ምርጫ ሊወዳደር ብሎ ያለ ማዕረጉ የሻምበል ማዕረግ፥ በዚያን ዘመን ሦስት ኮከብ አድርጎ ፎቶ መነሣቱ ተደረሰበት። ጉድ ሁሉ እያደር ነውና የሚወጣው በጥቆማ ተይዞ በውትድርና ደንብ ለ42 ቀናት ይመለሰኛል ማዕከላዊ እዝ ሆስፒታል በራፍ ላይ ያለችው እስር ቤት ሲሚንቶ ወለል ላይ ተኝቶ አይቼዋለሁ። ወቅቱን ጨርሶ እንደወጣም አእምሮው ስለተነካ ከሕፃን ልጁ ጋር መንገድ ዳር እርቃኑን ተኝቶ ታይቷል። እግዚአብሔር ሲቆጣ አይጣል ነው።

ስለዚህ ገደብ የሌለው የሥልጣን አመጣጥን በመርሳት መሥመር መልቀቅ ለዚህ ዓይነት ችግርና ዕብደት ይዳርጋል። በመሆኑም ጥንቃቄ ማድረግ ሊረሳ የማይገባ መመሪያችን መሆን አለበት። በዚህም ሁኔታ የወላጆች ጦስ ለልጆች የሚተርፍ ፍዳና በቀል ይከተላል። ሥልጣን ጥሩም መጥፎም ሊሆን ይችላል። ካላወቁበት ግን በእርግጥ ያጠፋል።

2.2.1. ሥልጣንና አጠቃቀሙ፡-

በአጠቃላይ ሥልጣን የእግዚአብሔር ነው። ማንም ሰው ይህንን ቢያውቅ ይጠቀማል። በማናቸውም ደረጃ ያሉ ባለሥልጣናት ቢሆኑ እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ የሠራውን ሊገነዘቡ ያስፈልጋል። ሥልጣን በግል ጉጉት፥ በሙያ ግዴታና በውክልና ማለትም በሌላ አካል ሊገኝ/ሊሰጥ ይችላል። ይህንን ግን አለመገንዘብ የሥልጣን ዘመንን ያሳጥራል። እንደተከበሩ ተዋርዶ መውረድም መሞትም አለ። እንደ ንጉሡ ናቡከደናፆር ያ የጠቀስኩት ፎካሪ ም/የመቶ አለቃ ያጋጠመው ይህ ነበር። እግዚአብሔር ከፍ ከፍ ያደርጋል፤ ያዋርዳልም። ስለዚህ ኃላፊነት የተሰጣቸው ባለ ሥልጣናት በዘመናቸው ድርሻቸውን ተወጥተው ቢያልፉ፥ ራሳቸው ከወቀሳ ድነው ትውልድን ከመወቀስ ያድናሉ። ደስ የሚለው ግን ማንም ቢሆን ከእግዚአብሔር አያመልጥም። ከሰማይ የሚመጣ የልዑሉ ትእዛዝ (ዳንኤል 4) ሲመጣ የወገብ ጅማት ይፈታል፤ ሥልጣንም ሁሉ ይሸሻል። እግዚአብሔር እንደ በሬ ንጉሥን እንኳን ሳር ማስበላት የሚችል ነው። ያ ነበር በታላቁ ንጉሥ ናቡከደናፆር የተከሰተው። በዘመናት ላይ የሚሠለጠነው ሲገለጽ በፊቱ የሚቆም አይኖርም።

2.2.2. የእግዚአብሔር ሥልጣን፡-

ይህ የእግዚአብሔር ሥልጣን፡-

- ፍጹም ነው፡- ከእርሱ በላይ ማንም የለም። በመሆኑም ፍጹምና ትክክለኛ ነው። እንከንም አይወጣለትም። (ኢዮብ 42ን ይመልከቱ)። በሮም ውስጥ የነበሩት ክርስቲያኖች ይህ ነገር ትልቅ ፈተናቸው ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 10፥9-10፤ «*ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር፥ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህ። ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና፥ በአፉም መስክሮ ይድናልና*» ይላል። በዚያን ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች በስደት ላይ ስለነበሩ በቄሳር ፊት አየቀረቡ፥ «ጌታ ማን ነው?» እየተባሉ እየተጠየቁ በፊቱ ያልፉ ነበር፥ «ቄሳር ነው» ያላሉት ሁሉ ለተራበ አንበሳ ይሰጡ እንደ ነበርና እንዲያውም ኒሮ በአትክልቱ ስፍራ በዘይት በተነከረ ጨርቅ ጠቅልሎ እንደ መብራት ይጠቀምባቸው እንደ ነበር ካለፈው ታሪክ ተረድተናል። የሰው ልጅ ጭካኔ የታየበት፥ ሰዎች የአውሬ ቆዳ ተሸፍነው በውሾች

የተቦጫጨቁበት ወቅትም ይታወሳል። የካታኩምቡ ሰማዕታት ምሥጢርም የዚህ ክስተት ገጽታና ውጤት ክፍል ነው።

– ዘላለማዊ ነው፦ ማቴዎስ 28፥18–20 «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ» ያለው ጌታ፥ በዚህ ሥልጣኑ የዘላለምን ወንጌል አደራ ለሰጣቸው ደቀ መዛሙርት እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ አብሯቸው እንደሚሆን ነግሯቸዋል። ለእነርሱ ብቻም አይደለም፥ ከታላቸው የተነሣ ለሚያምኑትና የእግዚአብሔርን የልጅነት ሥልጣን ለሚያገኙት ሁሉ እንጂ። ቃሉ እንደሚል፥ «ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው» ይላል። (ዮሐንስ 1፥12ን ይመልከቱ)።

–ያድናል፦ በ1ኛ ሳሙኤል 2፥6፥ በመዝሙር (98)፥1–3፥ «ለእግዚአብሔር አዲስ ምስጋናን አመስግኑ፥ እግዚአብሔር ተአምራትን አድርጎአልና፤ ቀኙ የተቀደሰም ክንዱ ለእርሱ ማዳን አደረገ። እግዚአብሔር ማዳኑን አስታወቀ» ይላል።

–ይገድላል/ያደቃል፦ 1ኛ ሳሙኤል 2፥6 እና 10፥ «እግዚአብሔር ይገድላል፥ ያድናልም፥ ወደ ሲኦል ያወርዳል፥ ያወጣል»።

–ያዋርዳል/ከፍም ያደርጋል፦ 1ኛ ሳሙኤል 2፥7–8፥ «እግዚአብሔር ድሀ ያደርጋል፥ ባለጠጋም ያደርጋል፤ ያዋርዳል፥ ደግሞም ከፍ ከፍ ያደርጋል፥» ሲል በመዝሙር (147)፥6 ውስጥ «እግዚአብሔር የዋሃንን ያነሣል፥ ኃጢአተኞን ግን እስከ ምድር ድረስ ያዋርዳል»።

–ነገሥታትን ይሽራል/ያስነሣል፦ «–––ጊዜያትንና ዘመናትን ይለውጣል፥ ነገሥታትን ያፈልሳል፥ ነገሥታትንም ያስነሣል» (ዳንኤል 2፥21ን ይመልከቱ)። ጥንት ብቻ አይደለም በዘመናችንም አድርጓል፤ ወደፊትም ያደርጋል።

በመሠረቱ እግዚአብሔር ሥልጣኑን ሁሉ የሚጠቀመው ለበጎና መልካም ነገር ነው። ስለሆነም ሥልጣኑን ለማንም ሳይሰጥ እንድናመልከውና እንድንሰግድለት ኃይሉን ያሳያል፤ ይገልጣልም። ምሕረቱን ያበዛል፤ ፍርድንም ያደርጋል። ሥልጣኑን ያጋራል፤ ያከፋፍላል። ዳሩ ግን የበላይነቱን ለማንም አይሰጥም። የሰው ልጆች ሙሉ ሥልጣን ቢሰጣቸው ምን እንደሚያደርጉ ያውቃልና ሁሉን በገደብ ያደርጋል። በዚችው በሚሰጠንም እንኳን አልቻል ብለናልና።

የእግዚአብሔር ሥልጣን በመንግሥት ደረጃ፥ በቤተ ክርስቲያንና በቤተ ሰብ ደረጃም እንኳን ቢሆን መጠኑ ይታያል። ሥልጣንን ግን በማናቸውም ስፍራ አላግባብ መጠቀም ያስጠይቃል። ሥልጣንን

አላግባቡ የተጠቀመ ሰይጣን፥ ሰዎችም በሥልጣን እንዲባልጉና አጠቃቀሙን አጓጉል እንዲያደርጉ ያደርጋቸዋል። ከጥንት ዘመን ጀምሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሥልጣን የባለጉ ሰዎች ነበሩ፤ አሁንም አሉ። አንዳንዶቹንማ እግዚአብሔር እስኪያጋልጣቸው ድረስ ምንም ማድረግ አይቻልም። ዝም ብሎ እያወደሱ መኖርም ሊያጋጥመን ይችላል። እንኳን ሰዎችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስንም በሥልጣኑ አላግባብ እንዲጠቀም በምድር በነበረበት ዘመን ሰይጣን ተፈታትኖታል። ይህም ምላሌ እንዲሆንልን በማቴዎስ 4፥1–10 የተጠቀሰውን መመልከት ይበቃል።

–<u>ድንጋዩን ዳቦ እንዲያደርግና እንዲበላ</u>፡– እርቦት እንደነበር ስላወቀ ይመስላል ይህንን ጥያቄ ያቀረበው። «የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፥ እነዚህን ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል አለው»። (ማቴዎስ 4፥3ን ይመልከቱ)። የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑንማ ራሱ ዲያቢሎስም ያውቃል እንኳንስ ጌታ። ግን ይህንን እያወቀ ተፈታተነው። በማቴዎስ 8፥29 ውስጥ፥ *«---ኢየሱስ ሆይ፥ የእግዚአብሔር ልጅ ከአንተ ጋር ምን አለን? ጊዜው ሳይደርስ ልታሠቃየን ወደዚህ መጣህን?»* እያሉ መጮኻቸው ራሱ ምስክር ነው። ዝናው በባሪያዎቹ እንጂ በአጋንንት መንገድ እንዲሰራጭ ያልፈለገ ጌታ አባሯቸዋል። አንዳንዴ ዲያቢሎስ ሰዎች በአቋራጭ መንገድ እየሄዱ ሥልጣናቸውን አላግባብ እንዲጠቀሙበት ያደርጋል። በአቋራጭ መንገድ የሚሄድ ሰው የራሱን ጥቅምና ክብር ወይም ዝና ብቻ ሲመለከት ገደል ይገባል።

–<u>አጉል እምነትና ድፍረት እንዲኖረው መመኘት</u>፡– በቁ. 6 እንደምናገኘው *«መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል፥ እግርህንም በድንጋይ ከቶ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል»* ብሎ ወደ መቅደስ ጫፍ ላይ ሊያቆመው እንዴት እንደ ወሰደው ይገርመኛል። እዚያም *«የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ ወደ ታች ራስህን ወርውር»* አለው። በጣም ጥሩ ጥቅስ ፈልጎ ነበር የጠቀሰለት። ዳሩ ግን ከመቅደስ ጫፍ ላይ አናዶ ወርውሮ ሊፈጠፍጠው የሚችል መስሎታል። የዲያቢሎስ ባሕርይ የሰዎችን ልጆች መጎተትና ማስቀረት ሲሳነው፥ በትዕቢት ገፍቶና ወጥሮ ይፈነግላቸዋል። ይሁን እንጂ ኢየሱስን ግን ሙሉ ለሙሉ ያወቀው አይመስለኝም። ስለዚህም ጌታ ሰው አይደለምና አልተገፋለትም።

ሰዎች በሥልጣን ሲባልጉ እንዲህ ነው የሚያደርጋቸው። ግን አለብኝ ብለው ራሳቸውን ወርውረው እንዲፈጠፈጡ ያደርጋል። ከመፈጠፈጣቸው በፊት ግን ጥቅስ ይሰጣቸዋል። ራሳቸውን ከፍ ከፍ እንዲያደርጉ፥ ያለ እነርሱ እንኳንስ ዓለም እግዚአብሔርም የሚኖር አይመስላቸውም። በዚህም የእግዚአብሔር ልጅ ፈተና ቀላል እንዳልነበር እንገነዘባለን። ሆኖም የመጣበትን ዓላማ የሚያውቅ በመሆኑ «*ጌታን አምላክህን አትፈታተነው*» ተብሎ ደግሞ ተጽፎአል» ብሎ መልሶታል።

–<u>ለዓለም መገዛት</u>፡– በመጨረሻም «እጅግ ረጅም ወደሆነ ተራራ ወሰደው፥ የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ– ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው» (ማቴዎስ 4፥9 ይመልከቱ)። ያኔ ነው ጌታ ኢየሱስ የተቆጣውና የተናደደው የሚመስለኝ። «*ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ፥ እርሱንም ብቻ አምልክ*» ተብሎ ተጽፎአልና» ብሎ አባረረው። በብልጭልጭ ነገር፥ በዚህች ቀሪ ዓለም ሃብትና ንብረት፥ በወርቅና በብር የዓለምን ጌታ ሊደልለው የቃጣ ዲያቢሎስ፥ እኛንማ ምንኛ ያብጠልጥለን ? በዚህ ምክንያት ይመስላል «ሲኦም ያልበላ ሲሻር ይቆጪዋል» ፈሊጥ የዘመኑን መሪዎች የሚፈታተነን። ስለዚህም ይመስላል ቅሌት ከመሪዎች አካባቢና መንደር አልርቅም ያለው። ይህ ችግር በማያምኑ ሰዎች ብቻ ላይሆን በሚያምኑም በግልጽ እየተከሰተ ያለ ችግር ሊሆን ይችላል።

ነቢዩ አሞጽ በነበረበት ዘመን የነበሩ የእስራኤል አለቆች «*–––ከዝሆን ጥርስ በተሠራ አልጋ ላይ ለምትተኙ፥ በምንጣፋችሁም ላይ ተደላድላችሁ ለምትቀመጡ፥ ከበጎችም መንጋ ጠቦትን ከጋጣም ውስጥ ጥጃን ለምትበሉ፥ በመሰንቆም ድምፅ ለምትንጫጩ፥ እንደ ዳዊትም የዜማን ዕቃ ለምታዘጋጁ፥ በፋጋ የወይን ጠጅ ለምትጠጡ፥ እጅግ ባማረ ሽቱም ለምትቀቡ፥ ስለ ዮሴፍ መከራ ግን ለማታዝኑ ለእናንተ ወዮላችሁ!*» (አሞጽ 6፥4–6ን ይመልከቱ)። ተደላድለው የተቀመጡ ሰዎች ለራሳቸው ብቻ ላይሆን ለሌሎችም ዕንቅፋት ይሆናሉ። ስተው ያስታሉ፤ የእግዚአብሔርንም መንገድ ያጣምማሉ። ሰውን ወደ ተራራ ጫፍ ላይ ወስደው ከከፍታው ላይ ያንከባልላሉ/ይወረውራሉ።

ጳውሎስ ለወጣቱ ጢሞቴዎስ እንዲህ ብሎት ነበር። «*አንተ ግን ትምህርቴንና አካሄዴን፥ አሳቤንም፥ እምነቴንም፥ ትዕግሥቴንም፥ ፍቅሬንም፥ መጽናቴንም፥ ስደቴንም፥ መከራዬንም ተከተልህ*» (2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥10–11ን ይመልከቱ)። እንደ ጠቀሳቸው ያሉ ነጠቦች

ለመሪዎች የሚያስፈልጉ ባሕርያት ናቸው። ለምሳሌ፦ ትምህርቴን (ብዙ አሳቾች በዘመኑ ስለነበሩ)፥ አካሄዴን (ጽናት የተሞላ ስለነበር)፥ እምነቴን (በእምነት የሚቀልዱ ዘባቾች ስለነበሩ)፥ ትዕግሥቴን (በደረሰበት ችግርና ፈተናና አብረውም የጸኑበትን ዘመን እንዲያስብ)፥ ፍቅር (ለነፍሳት የነበረውን ፍቅር)፥ ወዘተ. . . እንዲያሰላስል ይመክረው ነበር።

በ1ኛ መጽሐፉ በጻፈለት ደብዳቤም *«አንተ ግን፥ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከዚህ ሽሽ፤ ጽድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል እምነትንም ፍቅርንም መጽናትንም የዋህነትንም ተከተል። መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል፥ የተጠራህለትንም በብዙም ምስክሮች ፊት በመልካም መታመን የታመንህለትን የዘላለምን ሕይወት ያዝ።»* (1ኛ ጢሞቴዎስ 6፥11–12ን ይመልከቱ)። ወጣቱ ጢሞቴዎስ ለዚህ ዓለም የሚመች ሰውም እንዳይሆን በምዕራፍ 4፥7 አስገንዝቦታል። ለዚህ ዓለም የሚሸነፍ ሰው ለዲያቢሎስ ወድቆም ባይሆን በእጅ አዙር እየሰገደ መሆኑን በተለያዩ ሁኔታዎች እንረዳለን። ስለዚህ ይህ ነገር ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው።

ቅንነት በሌለው መንገድ ሃብትን ማካበትና አጭበርብረው ያገኙትን ሁሉ ጌታ ባርኮኛል እያሉ ማስወራት፥ በአሞጽ ዘመን የነበሩ አሰቆችን መሆን ነው። ለመንግሥት የሚገባ ግብርን በደንቡ መሠረት ባለመክፈል፥ በየጓዳው የሚደረግ ንግድም ከሌብነት ምንም አይተናነስም። በሌላ ሰው ላይ ተጫርቶ የምሥጢር ቁልፍ መግዛትና ጌታ ከጉሮሮው ነጥቆ ሰጠኝ ብሎ እንደበረከት ማስወራት ግልጽ ኃጢአት ነው። ጌታ እንዳዘዘ የቄሳርን ለቄሳር የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር መስጠት ተገቢና አስፈላጊም ነው። ለመሆኑ እኛ ሳንጠራ በሌሎች ላይ ስለምን እጃችንን እንጠቁማለን? ቤተ ክርስቲያን ሳትጠራ ዓለምስ እንዴት አድርጋ ልትጠራ ትችላለች? እንደዚህ ዓይነት ፈተና ሲመጣብን ሂድ አንተ ሰይጣን ካላልነው ባሪያ እንደሚያደርገን አልጠራጠርም።

2.3. የመሪ ተጠያቂነት

ተጠያቂነት (Accountability) ምንጊዜም የበላይ እንዳለ በማሰብ የተግባር ኃላፊነትና የሥልጣን ድርሻ የተሰጣቸው መሪዎች መልስ

የሚሰጡበት መድረክ ነው ማለት ይቻላል። ኃላፊነት ከሥልጣን ጋር ተዳምሮ የተሰጣቸው መሪዎች፥ ይህን የተጠያቂነት ድርሻ ብዙውን ጊዜ ይዘነጉታል። ሥልጣናቸው ከፍ ሲል ተጠያቂነት እንደዚያው እንደሚበዛባቸው አያስተውሉትም። ሳያውቁት ቀርተው አይመስለኝም። ዳሩ ግን ሥልጣኑ ሁልጊዜ ጎልቶ ስለሚታያቸው ተጠያቂነቱ ይዋጥባቸዋል።

ለምሳሌ፦ የቺሊው መሪ የነበሩት ጄኔራል አጉስቶ ፒኖሼ፥ የምዕራብ ጀርመኑ መራሔ መንግሥት የነበሩት ሔርማን ኩህል፥ የኮንጎሊዙ ሞቡቱ ሴቴሴኮ፥ የኮሪያው መሪ የነበሩት፥ የናይጀሪያው ጄኔራል ሳኒ አባቻና፥ ሌሎችም ልቆጥራቸው የማልችላቸው ሁሉ የእኛንም አገር መሪዎች ጨምሮ፥ ተጠያቂነትን በመዘንጋታቸው ወይም ለተጠያቂነት ዕድል ፈንታ ባለመስጠታቸው፥ የሕሊና ቁስለት፥ ስደት፥ ሞትና ውርደት፥ ከዚያም ሲያልፍ ወህኒና ግድያ ደርሶባቸዋል።

በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ ያሉ መሪዎችስ ከዚህ ዓይነት ልምምድ ምን ይማሩ ይሆን? ትምህርት ይቀስማሉ፥ ወይስ የጨለመ ሁሉ የሚነጋ፥ የነጋም የሚጨልም አይመስላቸውም? ስለምን ዘወትር ታሪክ ራሱን እንዲደግም ይፈቀድለታል? በማንኛውም ደረጃ ላይ ያለ ኃላፊ ተጠያቂነትን ካልዘነጋ ተግባሩን በሚገባ ሊወጣ ይችላል። ተጠያቂነትን መዘንጋት አብዛኛውን ጊዜ የሚመነጨው ከአምባገነኖችና ከማንአለብኝ ባዮች ነው። ሰው ተጠያቂነትን ሲዘነጋ ከበላዩ ማንም እንዳለ አያስብም። እንዲያውም ለዘላለም በምድር ላይ የሚኖር ሊመስለው ይችላል። የፈለገውን ይገድላል፤ የፈለገውን ያድናል። ያሻውን ይሾማል፤ ያሻውን ይሽራል። ድንገት ተጠያቂነት ሲመጣ ግን ውጪ ነፍስ፥ ግቢ ነፍስ ይሆንበታል።

ይህ ጉዳይስ በቤተ ክርስቲያን እንዴት ይታያል? የቤቱ ባለቤት ጌታ በዙፋኑ ላይ ነው። ሰው ባያይ እግዚአብሔር ያያልና ለምናደርገው ነገር ሁሉ፥ ክፉም ይሁን ደግ ወደ ፍርድ ወንበር ፊት መቅረብ ይኖራል። በምድር ላይ ጠያቂ የሌለን ታላቅ ሰው ብንሆንም ተጠያቂነት ፈጽሞ አይቀርም። የሰው ልጅ እንደ ቅጠል ሲረግፍ፥ የወላድ አንጀት ሲርገፈገፍ፥ አቤት ባይ ሲጠፋ፥ ክቡር የሆነ ሰው ቦታ ሲያጣ በአሁኑ ጊዜ ወህኒ የሚማቅቁት የቀድሞ ባለሥልጣናት የት ነበሩ? በመሠረቱ ፍጻሜ ሲዳረስና ጽዋ ሲሞላ ፍርዱ ከባድ ነው። ሁሉም በተራው ዕዳ ከፋይ ይሆናል።

ጌታ አንድ ጊዜ እንዲህ ብሎ ነበር፥ *«ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል»* (ማቴዎስ 12፥36)። ይህም ተጠያቂነትን ያመለክታል። በምሥጢር የምንናገረውን ወደ አደባባይ የሚያወጣ ጌታ ከእርሱ የሚሰወር ምንም

እንደሌለ አስረድቷል። ጳውሎስም በ2ኛ ቆሮንቶስ 5፡10 «መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ፥ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናል» ብሏል። ይህ እንግዲህ በቀጥታ የግል ተጠያቂነትን ያመለክታል። በዚህም ሁኔታ የማይቀር ነውና ሥራችን ይከተለናል (ሐዋርያው ዮሐንስ በራእይ 14፥13) እንደተናገረው። በክርስቶስ ዙፋን ፊትም መቅረብ አይቀሬ ነው።

ስለዚህ ጊዜ ሳለ መመለስ፥ ራሳችንንም መመርመርና ማስተካከል፥ መንገዳችንንም ማቅናት ይጠበቅብናል። አንዳንድ ጊዜ ኃላፊነትን ለሌሎች መስጠት ወይም ማከፋፈል ማለት ከተጠያቂነት ነፃ ያደርጋል ማለት እንዳልሆነ መረዳት ይገባል። ኃላፊነት መስጠት ማለት የነፃ መውጫ ዘዴ ሊሆን አይችልም። ይህም ከኃላፊነት ሽሽት (Abdication) ይባላል። ይህ ትልቅ ስሕተት ነው። የበላይ የሆነ መሪ ለሌላ ሥልጣኑን በማጋራት ኃላፊነት ቢሰጥና ነገሩ ቢበላሽ ያ የበላይ ኃላፊ ከተጠያቂነት አያመልጥም። ስለ ውክልና በመሪ ስሕተት ውስጥ የተሰጠውን መግለጫ ይመልከቱ።

በማንኛውም ቦታ ኃላፊነት ይኑረን፥ ሥልጣናችንም ገደብ አይኑረው፥ ጊዜው ሲደርስ ከተጠያቂነት አንድንም። በመሆኑም መሪዎች ተጠያቂነት እንዳለ ሁል ጊዜ ማሰብና መገንዘብ ይገባናል። ለምሳሌ፡– እነርሱ ባለፉበት እንኳን ማለፍ ያስፈራን የነበረው የጥቂት ዓመታት መሪዎቻችን ይኸው ተጠያቂነት ባመጣው መዘዝ በወህኒ ቤት እንዲማቅቁ አስገድዱቸዋል። ቢያንስ ቢያንስ ከዚህ መሰል ክስተት እንኳን ልንማር ይገባል። አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ይጠይቀን እንጂ ሲሉ ይሰማል። እግዚአብሔርማ አሳምሮ ይጠይቃል። እርሱ ግን ሲጠይቅ አያዳግምም። ይግባኝም የለበት። የሰበር ችሎትም የለም።

«ሰው ሆይ፥ መልካሙን ነግሮሃል፤ እግዚአብሔርም ከአንተ ዘንድ የሚሻው ምንድር ነው? ፍርድን ታደርግ ዘንድ፥ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፥ ከአምላክህም ጋር በትሕትና ትሄድ ዘንድ አይደለምን?» (ሚክያስ 6፥8 ይመልከቱ)።

በአጠቃላይ ቀመሩ ሲታይ **ኃላፊነት + ሥልጣን = ተጠያቂነት** ነው። ኃላፊነት ሰጥቶ ሥልጣንን መከልከል ደግሞ የጦር መሣሪያ አስይዞ ጥይት እንደ መከልከል ይቆጠራል። አብዛኛውን ጊዜ ፈሪና ንፉግ መሪዎች ይህንን ሲያደርጉ ይስተዋላሉ። የሚቀሙ ስለሚመስላቸው ሙሉዕ የሆነ ውክልና አይሰጡም።

በሚቀጥሉት ምዕራፎችም የእነዚህን ችግሮች ገጽታ መመልከት እንችላለን።

የመሪ ችግርና ስሕተት

በመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት መሪ ማለት እግዚአብሔር ወደ አሰበበት ዓላማና ውሳኔ ሕዝቡን የሚያድረስ ማለት ይሆናል። መሪ ሌላውን የሚረዳ፥ የሚያግዝና መንገድ የሚያሳይ እንጂ ሌሎችን በመጫን የራሱ ተገዢ በማድረግ በሥነ ልቡናዊ ተጽዕኖ ሥር የሚጥል ጌታና ሹም ማለት ግን አይደለም። መሪ እንደ ባሪያ አገልጋይ ነው። መንፈሳዊም ከሆነ ራሱ ባሪያ ነው። መሪ ሌላ ጌታ እንዳለው አውቆ ሌሎችን የሚያግዝና የሚረዳ፥ የታሰበበት ቦታ እንዲደርሱ መንገድ የሚያመቻች ነው። ይህ ካልሆነ ግን ችግር መከሰቱ አይቀርም።

3.1. የመሪ ችግር

መሪዎች እንደ ማንኛውም ሰው የሕይወት ውጣ ውረድና ችግር ሊኖርባቸው ይችላል። ለምሳሌ የታወቀው እንግሊዛዊ የሪቫይቫል ሰባኪ ጆን ዊስሊ እና ታዋቂው አሜሪካዊ መሪ አብርሃም ሊንከን በሚስቶቻቸው በኩል ከፍተኛ ችግር ነበረባቸው። ቢሊግርሃም እንኳን ዓለምን በወንጌል ሲደርሱ ቤታቸው ያለው ልጃቸው ፍራንክሊን እንዳባካኙ ልጅ አስቸጋሪ ነበር። ኔልሰን ማንዴላ የ27 ዓመታት እስርን ተቋቁሞ ደቡብ አፍሪካን ከአፓርታይድ ነፃ በማውጣት ቢረዳትም ባለቤቱን ዊኒ ማንዴላን አሸንፎ ትዳሩን ከመፍረስ ሊያድን አልቻለም።

በተለይ በአፍሪካ አህጉር የመሪዎች ችግር እጅግ ጎልቶ ይታያል። ይህ ችግራቸውም እንደሚባለው፥-

3.1.1. ራእይ ሳይኖራቸው ችግር ብቻ እየተከታተሉ በመንጎዳቸው፥-

እንደዚህ ያሉ መሪዎች ሁልጊዜ እንደ እሳት አደጋ ሠራተኛ ቃጠሎ ለማጥፋት የሚሯሯጡ ናቸው። በዚህም ምክንያት ድርጅታዊ ዕቅዶችን ሳይነድፉ፥ የችግሮችን ቅደም ተከተል ሳይለዩ ስለ ችግራቸው ብቻ ሲያስቡና ሲያሰላስሉ ዘመን ይፈጃሉ።

ኑሮአቸው በድንኳን ወይም በጎጆ እንደሚኖር ዘላን ያዩትን ሁሉ መከተል ቢሆንም ተረጋግተው እንዲሠሩ ግን የሚያበረታታቸው ያስፈልጋቸዋል። የራሳቸው ራእይ ሳይኖራቸው እንደ ሸቀጥ ከውጭ አስመጥተው (Import) ችርቻሮውን ሊተገብሩ ይመኛሉ።

3.1.2. በዓላማ ግልጽ አለመሆናቸው፡-

ይህ የዓላማ ግልጽነት አለመኖር ወዴት እንደሚሄዱ እንዳያውቁ ያስገድዳቸዋል/ ውሱንም ይሆናሉ። በአንድ ጊዜ ሁለት ቦታ መገኘት ያምራቸዋል። ተከተው ወይም ወከለው ለመሥራት ይፈራሉ። አንዱን አጥብቀው ሳይዙ ሌላውን ይመኛሉ። የተማረ ሰውም ስለሚጠሉ አያስጠጉም፤ ቢቻላቸው ያርቁታል፤ ያውም ካላጠፉት ማለት ነው።

3.1.3 ሙስናና ምዝበራ ስለሚጠናወታቸው፡-

በአምሳላቸው የተቀረጹ ሌሎች መሰሎችን ያፈራሉ። እነርሱም ፉርጎ ሆነው መከተልን ያዘወትራሉ። እንደሚባለውማ ጥሩ ሠሪ ያጣነው «እነርሱ ራሳቸው እንደ ተመሩ ስለሚመሩን» ነው።

3.1.4 ለቤተሰባቸው ጊዜ አለመስጠታቸው፡-

ብዙ አልቆየላቸውም እንጂ ፕሬዚዳንት ጆን ኤፍ. ኬኔዲ ቤተሰቡን በሚመለከት እንዲህ ይል ነበር። «ተግባሬ/ሥራዬ ቤተሰቤ ነው፥ ቤተሰቤም ተግባሬ ነው»–"My business is my family, and my family is my business"[1]. መሪ ቤተሰቡን ችላ ካለ አለቀለት ማለት ነው። ዘወትር በሰቀቀንና በፍርሃት ስለሚኖሩ መልካም እንቅልፍንና ዕረፍትን አያውቁም። እስከ ሞት ድረስ (በድዳቸው እንደሚባለው) መምራት/መግዛት ስለሚፈልጉና ስለሚመኙ አእምሮአቸው በሁከትና በጭንቀት የተሞላ ነው። ከዚህም የተነሣ ጨካኞች ናቸው። የሕዝብ ጩኸትና እሮሮ አይሰማቸውም።

3.1.5 ለሰው ልጅ ያላቸው አክብሮትና የሚሰጡት ቦታ (Value) ዝቅተኛ መሆኑ፡-

ስለ ሕዝባቸው ብዙም አይገዳቸውም። በራሳቸው ፍላጎት ዙሪያ የተጠላለፉ ናቸው። ከመሾማቸው በፊት ግን ስለ ሕዝቡ እሮሮ ብዙ ብዙ ያወራሉ፤ ይጮኻሉ። ሲሾሙ ግን ይረሱታል። ሕዝቡንም ለፍላጎታቸው መወጣጫ መሰላል ያደርጉታል። በኋላም ውረዱ ሲባሉ ይሞቷታል እንጂ ቦታቸውን አይለቁም። አብዛኛውን ጊዜ መፈንቅለ-መንግሥት ነው ወንበራቸውን የሚያስለቅቃቸው። ምናልባትም ወንበራቸውን ለመልቀቅ የሚያስፈራቸው የሠሩት ተግባር ስላለ ሊሆን ይችላል። በመሆኑም በኋላ የሚመጣው ተተኪ ትውልድ አይምራቸውም። ሲበዛ ይገድላቸዋል፥ ወይም ያሳድዳቸዋል፥ ወይም ግዞተኛና የዕድሜ ልክ እስረኛ ያደርጋቸዋል።

3.1.6 ከሌሎች ድካም አለመማርና ድካሙን መድገም፡-

ሞዴል ሆኖ የሚታያቸው ድካም ብቻ ይሆንና እነርሱም ያንኑ ይሆናሉ። ምሳሌያዊ የሚሆን መሪ ያጣሉ። በመጠይቁ ውስጥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጥሩ መሪ/ ምሳሌያዊ የሚሆን (Reference) አለዎት? ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ [45.2%] መልስ የለኝም የሚል ነበር። ነገሩ በጣም የሚገርም ሆኖ ነው ያገኘሁት። ይህ ለእኔ ወዮ! የሚያሰኝ ነው። በተረፈ ይህ ሁኔታ በሁሉም ደረጃ ያሉትን መሪዎች ሊመለከት ይችላል። ቢቻል መሪ ሌሎችን ሳይሆን ራሱን ቢሆን ይመረጣል።

3.1.7. ከመሾማቸው የእነርሱ የተፈጥሮ ውሕድ ያልሆነ የባሕርይ ለውጥ ማሳየታቸው፡-

ለመልካም ሳይሆን ለጥፋት ባሕርያቸውን ይቀይራሉ። አምባገነን ይሆኑና እኔ ያልኩት ብቻ ይፈጸም ይላሉ። ያሉትን ሁሉ ደግሞ ለመፈጸም የሚከብደው ሲኖር በሚያጅቧቸው የክብር ዘቦች (Palace Guards) /ወታደሮች ማለት አይደለም/ ራሳቸውን ይከብባሉ። ከዚህም የተነሣ እሺ እሺ የማይላቸውን ይገፋሉ። ሲከፋም የአውሬነት ባሕርይ ይለማመዳሉ። ገና ወንበሩ ላይ ሲቀመጡ ኮራ፥ ረጋ፥ ጀነን፥ ቀብረር፥ ፈራ ተባ፥ ቆጣ ቆጣ፥ ሲናገሩም የውሸት ሳቅ ለመሳቅ ፈገግ ይላሉ። በየንግግራቸውም ጣልቃ እያስገቡ «ኧኧ---እእ---ኧኧ---ኧእ» ማለት ያበዛሉ።

ይህ ምን ማለት እንደሆነ ባይገባኝም የሚያዳምጣቸውን ሲያለለቹ ግን ይሰማል፤ ይታያል። ከዚያ በኋላ ጥላቸውንም እንኳን ማመን ያቅታቸዋል። መጪው ያስፈራቸዋል። ስለወደፊቱም

የሚነግራቸው ሰውም ሆነ ሌላ ፍጡር ይፈልጋሉ። ስለሆነም ነው አስማትና ጠንቋይ አዘውታሪ ይሆናሉ የሚባለው። ይህ ዓይነት ክስተት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንኳን ተከስቷል። ንጉሡ ሳኦልን ልብ ይሏል። አዶልፍ ሂትለርም አስማተኞች ታንቆ ከመሞት አላዳኑትም እንጂ መኖርማ ነበሩት። በማንኛውም ደረጃ ያለ መሪ በዚህ ሊፈተን ይችል ይሆናል። ራሱን ገዝቶ ይህንን ደካማ አስተሳሰብ ያሸነፈ መሪ የታደለ ነው። እግዚአብሔርም በእርሱ ይከብራል።

3.1.8 ውድቀትንና ሽንፈትን መፍራታቸው፡-

መውደቅ ካለ መነሣትም ይኖራል። ፈሪ ሰው ግን ውድቀቱ እዚያው ያስተኛዋል። ፈሪ ሰው እንዳጋጣሚ እንኳን ከጣለ አይነሣም፤ የሚከተለውን ይፈራልና። ታላቁ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የነበረው አብርሃም ሊንከን መሠረቱ ከገበሬ ቤተሰብ ነበር ይባላል። ከ31 ዓመቱ እስከ 58 ዓመቱ ድረስ ለ27 ወይም 28 ዓመታት ያህል ተደጋጋሚ ውጣ ውረድን አይቶ፥ በተለያዩ የውድድር መድረኮች ተሸንፎና ወድቆ፥ ባለቤቱ ሞታበትና ጤናውም እንኳን ታውኮ (የአእምሮ በሽታ ችግር ዓይነት (Nervous Breakdown) ገጥሞት)፥ ተስፋ ባለመቁረጡ ብቻ በመጨረሻ በ1860 ዓ. ም. ፕሬዚዳንት ሊሆን ችሏል። እንዲያውም ምርጥና ታላቅ ፕሬዚዳንት ሆኗል። በእውነቱ ያልደረሰበት የፈተና ዓይነት አልነበረም ማለት ይቻላል።

በመሠረቱ መሪ በራእይ የሚጓዝና ተስፋ የማይቆርጥ/ቆራጥ ሰው ነው። ራእዩም የራሱ እንጂ በሌሎች ዕይታ አይመላለስም። አትሌቶቻችን አንዴና ሁለቴ ባጋጠማቸው ሽንፈት ተስፋ ቆርጠው ቢሆን ኖሮ በቅርቡ በሲዲኒው ኦሎምፒክ ያየነውን ደስታ በሕይወታችን ሳናይ እናልፍ ነበር። «ደራርቱ በቅቶላታል» ሲባልም ሰምቼ ነበር። ያልበቃላት ጽኑ አትሌት ግን ማንነቷን አስመስክራለች። ደስታችንንም እጥፍ ድርብ አድርጋዋለች።

«ይቻላል!» የሚል መሪ ቃል/መፈክር (Theme) ይዘው በጥረታቸውና በእግዚአብሔር እርዳታ (ብዙ ሰው ይጸልይላቸው ስለ ነበር፥ እነርሱም እንዳሉትና እንዳመኑት) ተችሏቸው ተመልሰዋል። በረሃብ፥ በጦርነትና በፍትሕ እጦት ያዘነውንና የጠወለገውን መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር አስፈንጥዘዋል። ይቻላል ያሉት፥ ናፖሊዎን ቦኔፓርት "The word impossible is not in my Dictionary"፥ «በመዝገበ ቃላቴ ውስጥ አይቻልም የሚባል ቃል

የለም» እንዳለው ግን አይመስለኝም። የእርሱ ትዕቢት ነው፤ የእነርሱ ግን ተስፋና ጽናት ነው። ዶ/ር ወ/መስቀል ኮስትሬም ይህን የሻለቃ ኃይሌን የአንድ ጊዜ ልምድ በመጥቀስ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ አረጋግጠዋል።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እኔ በበኩሌ በዕድሜዬ እንደዚህ ያለ አቀባበልና ያን ያህል ሕዝብ ግልብጥ ብሎ የወጣበትን አይቼም ሰምቼም አላውቅም። የአዲስ ዘመን ጋዜጠኛም «ሕይወት» በሚለው አምዱ እሑድ መስከረም 28 ቀን 1993 ዓ. ም. ታትሞ በወጣው ጋዜጣ ላይ «ለአትሌቶቻችን ፍቅር ዘነበላቸው» ብሏል። ይህንን ሁሉ ሳገናዝብ ያለ ቀበሌ ቅስቀሳና ግዳጅ የሕዝብ ስሜት የሚስተናገደውስ መቼ ይሆን? ብዬ ጠይቄአለሁ። መሪዎች ያውም የሀገር ከዚህ ምን ይማሩ ይሆን? ይህንን የቤት ሥራ ከቻሉት ለእነርሱ ትቼዋለሁ። ያ አቀባበል ማስተዋል ላለው ሰው የሚያስቀናና የሚያስጎመጅም መሆን አለበት።

አንድ አባባል አለ፡– «ሁለት እስረኞች ወህኒ ቤት ውስጥ ሆነው በቀዳዳ ወደ ውጪ ሲመለከቱ፥ አንደኛው ጭቃ አየ። ሌላኛው ግን ከዋክብት አየ»። ታዲያ የትኛው ይሻላል? እንደ እኔ ከሆነ ከዋክብት ያየው ይሻላል። ቢያንስ በልቡ ተስፋ ይፈነጥቃሉ። ጭቃ ያየው ግን ራሱንም እንደ ጭቃ ከመቁጠር አይመለስም። ለዘመናት እዚያው ወህኒ ቤት ቆይቶ የሚሞት ይመስለዋል። ይህ አባባል የወህኒ ቤትን ደጃፍ ለረገጠ ይገባዋል።

3.1.9 እንዳወሩና እንደ ጀመሩ አለመጨረስ፡–

ለሀገርና ለወገን ተቆርቋሪ ሆነው «ምን ነው ለአንድ ቀን እኔ መሪ በሆንኩ!» ሲሉ ከርመው አጋጣሚ ለዚያ ሲያበቃቸው፥ ቀድሞ ያስቡት፥ ያልሙትና ይመኙት የነበረውን መልካም ተግባር ይለውጣሉ። ስለዚህ ነበር እነ ሌኒን ከኅብረተሰብ መገለል/መገንጠል (Alienation from the Society) ብለው ይናገሩ የነበሩት። እውነተኛ መሪ እንደ ኃይሌ ገ/ሥላሴ አጀማመሩን ሳይሆን አጨራረሱን የሚያሳምር ነው። ይህ አትሌት «ጉደኛ» አትሌት ነው። ያዝልቅለት እንጂ ማንኛውም የኢትዮጵያ መሪ እንደ እርሱ የሕዝብ ፍቅር ያገኘ መኖሩን እጠራጠራለሁ። የተናገረውን ያደረገ አትሌት ነበር። ያ ነው እንግዲህ የሕዝብ አደራ የሚከብደው መሪ ማለት። ምኞትና ተግባር/ ድርጊት ሳይገናኙ የሚተላለፉበት መሪ ከሰው ሁሉ ምስኪን የሆነ ሰው ነው።

በአገራችን እገሌ እንዴት ነው? ተብሎ ሲጠየቅ፥ «እንጃ ጥሩ ጀምሯል፥ መጨረሻውን እግዚአብሔር ይወቅ» ነው መልሳችን። ይህ

አባባል በሁሉም ደረጃ ላሉት መሪዎች ሊነገር መስማታችን አይቀርም። ሰዎች ገና ሲጀምሩ አጨራረሳቸው ያስፈራናል። በሀገር ደረጃም የጠላነው መንግሥት ወድቆ አዲሱ ሲተካ ከልምድ ባገኘነው እውቀት ሁል ጊዜ መጠራጠራችን አይቀርም። ብዙ ያወራውም አዲሱ መንግሥት ሰንበትበት ሲል ያው ይሆናል። «የፈሩት ይደርሳል፥ የጠሉት ይወርሳል» እንደሚባለው ይህ ነገር ያጋጥመናል። ከዚህ ግን መዳን አይቻልም ወይ? ዶ/ር ኮስታ እንዳሉት «ታላላቅ መሪዎች ታላቅነታቸው የሚታወቀው በእግዚአብሔር ፊት ራሳቸውን ትንሽ ማድረግ ሲችሉ ነው።»[3]

የተናገሩትን የሚያደርጉ እንደነ ኃይሌ ገ/ሥላሴ ያሉ አትሌቶች ግን፥ *«---ንጉሥ ሊያከብረው ለሚወድደው ሰው ምን ይደረግለታል?»* ብሎ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ (ነህምያ 6፥6) አርጤክስስ ሐማን እንደጠየቀው፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአትሌቶቻችን ተገቢውን መልስ ሰጥቷል። በማንኛውም ደረጃ ያሉ መሪዎቻችንስ ከዚህ ሁኔታ ምን ተምረው ይሆን? በእርግጥ ደስ እንደሚላቸው እገምታለሁ፤ ይሁን እንጂ እንደዚህ ለመከበርና ለመወደስ የተናገሩትን ማድረግና ለባንዲራ መሮጥ ያስፈልጋል። ለመሆኑ በአሁኒቱ ኢትዮጵያ ታሪክ የዚህ ዓይነት አቀባበልና አከባበር የተደረገለት፥ መስቀል አደባባይ ብቻ ሳይሆን ሕዝብ በነቂስ በየአካባቢው ጭምር ወጥቶ የተቀበለው/የተቀበላቸው መሪዎች ይገኙ ይሆን? በእርግጥ የአትሌቶቹ እንባ በሕዝብ ፍቅርና ስሜት ታብሷል። የአገር ስሜትና ፍቅር ነውና፥ ያለቀሱት አትሌቶቹ ብቻ አይደሉም። በዚህም በአገር ቤት ያሉት ብዙ ወገኖቻቸውንም የባንዲራና የአገር ፍቅር አስለቅሷቸዋል።

3.1.10 በሕዝብ የበላይነትና አዋቂነት አለማመን፡-

አብዛኛውን ጊዜ መሪዎች በተለይም የአፍሪቃ መሪዎች ሕዝቡ የሚያውቅ አይመስላቸውም። እነርሱ በማወቅና ከሌላ በመሻል መሪ የሆኑ ይመስላቸዋል። ከእነርሱ በእጥፍ የተሻሉ ሰዎች በሕዝቡ መካከል እንዳሉና እንደሚኖሩ አይገነዘቡም። ስለሆነም ይህን «የዋህ ሕዝብ ሊጠነቀቁለት እያስመሰሉ» በበታችኝነትና በዝቅተኝነት ስሜት ሊገዙት ይመኛሉ። «ሕዝቡ አያውቅም ይላሉ፥ ፈታትቶ ሊገጣጥማቸው እንደሚችል» ግን ማን ባስረዳቸው?

ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ዓይነ ስውር መሪያቸውን በእጃቸው ጭብጥ አድርገው ይዘው ይደበድቡት ነበር። እርሱም ስለተያዘ ጊዜ እየጠበቀ ይመስላል፥ ሳይወድ ግድ ነበርና ወደሚለምኑበት ሁሉ

ያደርሳቸው ነበር። ታዲያ አንድ ምሽት አጥብቀው ይዘው ሲደበድቡት እንመለከት ነበር። ይቆነጥጡትም ነበር። ጥቂትም ሳይቆዩ ድንገት ያችን መከረኛ ሣንቲም የሚወረውርላቸው ሰው መጥቶ ሣንቲሟን ሲጥልላቸው ልጁን ለቅቀውት ኖሯል ሸሽቶ አመለጣቸው። ኃላፊ የሆነ/አለቃ እስከ ጊዜው ሊጨቆን፥ ሊበደል፥ ሊደበደብ ይችል ይሆናል። ሆኖም ግን ዘለቄታ የለውም። ተመሪው በመሪው ላይ የተደገፈ ጥገኛ ነበር ማለት ይቻላል። በሕዝብን ግን እንደዚህ ማድረግ አይቻልም። በደምሳሳው መሪዎች ትክክለኛ መረዳት የተሳናቸው ይመስላል። መሪ መሆን ችግሩ ምን ይሆን? ለምን ሌላውን አይሰማም?

ሕዝብ አያውቅም አይባልም። በሀገር ደረጃ ሕዝቡ፥ በቤተ ክርስቲያንም ምእመኑ ምንም አያውቅም ተብሎ አይገመትም። ያውቃል እንጂ! አሳምሮ ይገነዘባል። ለጊዜው ፈርቶ ሊገዛ ይችል ይሆናል– እንደዚያ ልጅ። አንድ ምቹ ቀን ሲመጣ በቁጣ ገንፍሎ አደጋ ያደርሳል። ሕዝቡ ነገርን በሆዱ ማስቀመጡ «ተው ቻለው ሆዴ» ማለቱ ደንቆሮ አያሰኘውም። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ያንን ሁኔታ በግልጽ አሳይቷል። የሚወዱትና የሚወዳቸው ሕዝባቸው «ሌባ! ሌባ!» እያለ ከዙፋን መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ. ም. ጥዋት ላይ አውርዱቸዋል።

ቀጥሎም የነበረው ወታደራዊ መንግሥት ያው ነበር። አንድ ጊዜ ተሰልፈን ወደ አብዮት አደባባይ /የአሁኑ መስቀል አደባባይ/ ስንሄድ አንዲት የቀበሌ አውራጅ አብዮቷን ስታወድስ «እኔ ለአብዮቴ ይብላኝ አሞራ» ትላለች። በኋላም አናደደችንና ይብላሽ አልናት። በእርግጥ መስማቷን አላውቅም። ውሸቷን እንደነበር ግን ያስታውቅባታል። ይህን ያመጣሁት የማናውቀውን ነገር ዝም ብሎ ማወደስ ተገቢ አለመሆኑን ለማስገንዘብ ነው። «ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ» እንደሚባለው ነበርና ምንም ሳናይ ዘመናት አለፉ። አሁንስ እንዴት ይሆን?

ስለዚህ መሪ ከተመሪ ጋር የቀረበ ግንኙነትና መደጋገፍ (Interdependence) ከሌለው፥ አደጋው የከፋ ነው። አንዱ ከአንዱ ጋር የመደጋገፍ ባሕርይ ማሳየት የሚጠበቅና እጅግም አስፈላጊ ነገር ነው። አለበለዚያ «ቅዝምዝም ወዲያ ፍየል ወዲህ» ሆኖ ይቀራል። ይህ እንግዲህ ትልቅ የመሪዎች ስሕተት ነው። ሕዝብና መንግሥትም በዚህ ሁኔታ ይራራቃል።

3.2. የመሪ ስሕተት

እንደ ማንኛውም ሰው ሁሉ መሪዎችም ስሕተት ሊፈጽሙ ይችላሉ። ዳሩ ግን ከችግራቸው ተምረው ራሳቸውን የሚያርሙ ሰዎች የታደሉ ናቸው። እንደ ችግር ሁሉ ድሎትም ወደ ስሕተት ስለሚመራ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ የንጉሥ ልጅ የሠራውን ስሕተት እስቲ እንመልከት።

በ1ኛ ነገሥት 12 ውስጥ የተጠቀሰው ሮብዓም የተባለው የጥበበኛው ንጉሥ የሰሎሞን ልጅ ነበር። አባቱ ከሞተ በኋላ እስራኤል ሁሉ ያነግሡት ዘንድ ሴኬም ወደሚባል ቦታ ሄደ። ሕዝቡም ወደ እርሱ መጥተው፥ «አባትህ---በላያችን የጫነውን የከበደውን ቀንበር አቃልልልን፥ እኛም እንገዛልሃለን ብለው ተናገሩት» (ቁጥር 4ን ይመልከቱ)። እርሱም አባቱ ሰሎሞን በሕይወት በነበረበት ዘመን በፊቱ ይቆሙ ከነበሩት ሽማግሌዎች ጋር «ለዚህ ሕዝብ እመልስለት ዘንድ የምትመክሩኝ ምንድር ነው?» ብሎ ጠየቀ። ሽማግሌዎቹም በቁጥር 7 ላይ እንደተጠቀሰው፥ *«ለዚህ ሕዝብ አሁን ባሪያ ብትሆን፥ ብትገዛላቸውም፥ መልሰህም በገርነት ብትናገራቸው፥ በዘመኑ ሁሉ ባሪያዎች ይሆኑልሃል»* ብለው ተናገሩት። በእርሱ ደረጃ በቤተ መንግሥት ሥልጣን ሳለ ባሪያ የሚሆን አገልጋይ መሪ (Servant leader) የሚባለው ዓይነት ብቻ ነው። ይህን መሰል መሪ ውድ የሆነና በቀላሉ የማይገኝም ነው።

አገልጋይ መሪን «ቲዎሪ-አር» (Theory -R- Management)* የሚባለው ዘመናዊ የሥራ አመራር ስልት የሚደግፈው ሆኖ፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረውና በተግባርም ያሳያው ትምህርት ነው። በኋላ ግን ወጣቱ ንጉሥ ሮብዓም ሽማግሌዎቹ የመከሩትን ችላ ብሎ ወደ መሰሎቹ ሄደ። ጓደኞቹም እንዲህ ብለው መከሩት፥ *«---እኔ ግን በቀንበራችሁ ላይ እጨምራለሁ፥ አባቴ በአለንጋ ገርፎአችኋል፥ እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለሁ በላቸው»* አሉት። (ቁጥር 11ን ይመልከቱ)። የአባቱን ባለሟሎችና ነባር ሽማግሌዎች ንቆና ትቶ ከአብሮ አደጎቹ ተመካክሮ የእስራኤልን መንግሥት ለመከፋፈል አበቃው። በኋላም የአባቱን የዳዊትን ጎሣ ማለትም የይሁዳን ነገድ

---

* Wayne T. Alderson & Nancy McDonnel Anderson, *Theory R Management*, (Thomas Nelson Pub.,1994), P. 28. Talks about relational management principles.

ብቻ ይዞ ቀረ። ከዚህም የተነሣ እስራኤል በዳዊት ቤት ላይ ሸፈተ። ይህ መሪ የሚፈጥረው ደንበኛ ስሕተት ነው ማለት ይቻላል።

ስለዚህ አማካሪ እንኳን በውል ለይቶ ማወቅ እጅግ ጠቃሚ ነው። በዚህ አጋጣሚ አማካሪ የሚያበዙና የክብር ዘቦችን (Palace Guards) አስተያየት ለሚጠይቁ ሁሉ ምክር ማስተላለፍ እወዳለሁ። መመካከር መልካም ቢሆንም አጉል መካሪ አገር እንደሚያጠፋ ማወቅ ይገባል።

እንደ ሃንስ ፊንዝል (Hans Finzel)* አገላለጽ መሪዎች ቢያንስ አሥር ስሕተቶችን ይፈጽማሉ። ስሕተቱን ለጊዜው በአሥር ቢያጠቃልሉትም፥ እንደ እውነቱ ከሆነ በሁለት አሥርታትም ሊቆጠሩ ይችላሉ። ይህንን ሁሉ ስሕተት ግን የምንፈጽመው ምናልባትም «እንደ ተመራን ስለምንመራ» ብቻ ሊሆን ይችላል። ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያችን አገልጋይ (Servant Leader) እየተባለ ተደጋግሞ ሲገለጽ ይሰማል። እውነተኛ መሆኑን ግን እንደ አሁኑ ዘመን ጠርጥሬ አላውቅም። ሁሉም መሪ መሆን ፈልጎ ተመሪ የጠፋበት ዘመን ቢኖር አሁን ነው። ሁሉ መሪ ከሆነ ደግሞ አወቅሁሽ ናቅሁሽ የሚመጣ ይመስለኛል። የመጣው ሁሉ «አዲሲቱ ኢትዮጵያ» ይለናል። ዳሩ ግን ከአርባዎቹ በዘለቀ ዕድሜዬ አገሪቱ ያው ናት።

ከዚህ በመቀጠል ሚ/ር ሃንስ የጠቀሷቸውን የመሪ ስሕተቶችንና ሌሎችንም እኔ የተገነዘብኳቸውን በማዳቀል እንደሚከተለው አቀርባለሁ። ይህ ለስሕተት የተጋለጥ መሪ፡-

2.1 የገዢ ባሕርይ ያለው (Top-Down):-

የዚህ ዓይነት ባሕርይ ያለው ሰው የማያዳምጥ፥ ሥልጣንና ኃላፊነትን የማይቀበል እምቢተኛ ነው። ውሳኔውን ማንም እንዲቃወምበት የማይፈልግና የሚያውቁና የተማሩ ሰዎች ጠላቶቹ የሆኑበት ዓይነት ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑን ኮሚኒስት አገሮች የሌላ አገር ጋዜጣ ወደ አገራቸው እንዳይገባና ሕዝብ ሬዲዮ እንኳን እንዳያዳምጥ የሚያጣጥሉበት ሥርዓት ነው። ከአውሮፓ አገር የሚገቡ ጋዜጦችና መጽሔቶች እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ በጣም የሚፈሯቸው ጠላቶቻቸው ነበሩ። የፈሩት አልቀረም

---

* Hans Finzel, *The Top Ten Mistakes Leaders Make*, (Wheaton, IL.,Victor Books, 1994).

ፈራረሱ፤ ዳግም ላይመለሱ ተንኮታኮቱ። በእኛም አገር ቢሆን ይህን ድርጊት በመጠኑ በነበሩት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ተገንዝበናል። አዶልፍ ሂትለር ስለ ፕሮፓጋንዳ ሲናገር «ባልተማሩ ሰዎች መካከል መጠቀም ያስፈልጋል» ይል ነበር። ምክንያቱም ሌሎቹማ ያውቁበታልና ነው።

እንደዚህ ያሉ መሪዎች ሁሉ ሰው እንዲያገለግላቸው ይመኛሉ፤ ይፈልጋሉም። መሪ መሆን ማገልገል ሳይሆን መገልገል ነው ብለው ያስባሉ። ይህ እንግዲህ ፈርዖናዊና ፊውዳላዊ አገዛዝን ያስታውሰናል። አገልጋይ የሆነ መሪ ግን ሌሎችን እያሠራ ራሱ የሚሠራ፥ ሲቆሽሹ አብሯቸው የሚቆሽሽ፥ የገቡበት የሚገባ፥ የወጡበት የሚወጣ እንጂ ቦርሳ አሸክሞ፥ ካፖርት ማስያዝና መኮፈስ አይደለም። ለምሳሌ፦ በቅርቡ አንድ የወዛደሮች አለቃ የተባለ ሰው እነርሱ ስሚንቶ ሲያቦኩ እርሱ ውጭ ወንበር ላይ ተቀምጦ ሲያዛቸው አይተን ተገርመናል። ይህ እንግዲህ ዘመኑ ያለፈበት የአመራርና የአገዛዝ ስልት ነው።

3.2.2. ከሰዎች ይልቅ ወረቀት ማስቀደም፦

የሰው ልጆችን ልዕልና፥ ክቡርነት/ውድ ዋጋ ወይንም እሴት (Value) ያልተገነዘብ ነው። በሰዎች ለሰዎች ግንኙነትና መጠጋጋት፥ መግባባትና መከባበር፥ ለሰው ስፍራ ለመስጠት እምብዛም አይጨነቅም። የምርት ግብዓት ዓላማቸው ሆኖ ሰብዓዊነት ግን ትዝም አይላቸው። ይህ ታዲያ ከፍተኛ ችግር ነው። ጥሩ መሪዎች ግን ከሰዎች ጋር ጊዜ ያጠፋሉ/ያሳልፋሉ፤ ለሰዎችም የሚሆን ጊዜ ያስተርፋሉ ይባላል። ሕዝቡን ያዳምጣሉ፤ ይነግሩታልም። ከራስ አልፎ የሌላ ሰው ችግር መስማትና ችግሩንም ለመፍታት መሞከር ትልቅ ስጦታ ነው።

ስለ ሰው የሚያስብ ሰው ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው፥ «እኛም በክርስቶስ ፍጹም የሚሆን ሰውን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ ሰውን ሁሉ እየገሠጽን ሰውን ሁሉ በጥበብ ሁሉ እያስተማርን የምንሰብከው እርሱ ነው። ለዚህም ነገር ደግሞ በእኔ በኃይል እንደሚሠራ እንደ አሠራሩ እየተጋደልሁ እደክማለሁ።» (ቆላስያስ 1፥28-29ን ይመልከቱ)። በሉቃስ 4፥40 ውስጥ ደግሞ እንደምናነበው፥ «ፀሐይ በገባ ጊዜ (ማታ ማለት ነው) በልዩ ልዩ ደዌ የተያዙ በሽተኞችን ሁሉ ወደ እርሱ አመጡአቸው፤ እርሱም በእያንዳንዳቸው ላይ እጁን ጭኖ ፈወሳቸው» ይላል። ጌታ ለእያንዳንዱ ጊዜ ሰጥቶ ነበር የፈወሳቸው። አዲሱ የ(ቲዎሪ አር) ሥራ አመራር ስልትም ይህንን ሙሉ በሙሉ ይደግፋል።

3.2.3. ሰዎችን አለማበረታታትና ማረጋገጫ አለመስጠት፡-

ሰዎች ያበረታታናቸውን እንጂ የጨቀጨቅናቸውን አይሆኑም። ገንዘብ ከሚያነቃቃው ይልቅ ማበረታታት የሚያነቃቃው ይበልጣል። ጎበዝ፥ በርታ፥ አንተ ታማኝ ባሪያ መባል የሚናፍቁ ብዙዎች ናቸው። ሰዎችን በተለያየ ሁኔታ ልናበረታታ እንችላለን። ችግራቸውን እንኳን ረጋ ብለን በማዳመጥ፥ የምንችልም ከሆነ ብናጽናናና ብናደፋፍር ይህ ትልቅ ፈውስ ነው። ብዙ ሰዎች ጆሮ የሚሰጣቸው እያጡ ነው። አንድ ጊዜ ባክ ሮጀርስ የሚባል መሪ እንደዚህ ብሏል፤ ሰዎች ጥሩ ጥሩ ተግባር ካከናወኑ፡-

- ከቢሮ ወጥተህ ወደ እነርሱ ሄደህ አመስግናቸው።
- ጥሩ ሥራ/ተግባር ምሥጢር መሆን የለበትም።
- ስለዚህ በግልጽ ሰው ፊት መመስገን ይገባቸዋል። ይህ በተለይ በህገራችን ያልተለመደ በመሆኑ መሞከሩ አይከፋም እላለሁ። የሚታየው ሥነ ልቡናዊ መነቃቃት በቀላል የሚገመት አይሆንም።

3.2.4. አዲስ አሳብ የሚያፈልቁትን አለመቀበልና እንደ ልዩ ሰው ማየት፡-

በዚህ ረገድ እነ ሶቅራጥስ፥ ፕሌቶ፥ ጋሊሊዮ፥ ሐዋርያው ጳውሎስ፥ ማርቲን ሉተር፥ ካልቪን፥ ወዘተ... ብዙ ብዙ አሳቦችን አፍልቀው እንደ እብድም ተቆጥረው አልፈዋል። ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ወይም የራስ ልምምድ ሰውን ሊያስሩ አይገባም። አዳዲስ አሳቦች አይጠሉም፤ ግትር ሳንሆን፥ መመሪያዎችና ሕግጋት በሰው ነውና የተቀረጹት ለማስተካከል መጣር ያስፈልጋል። እንደ ሃንስ ፌንዝል ቤተሰብ ማንኛውንም ሰው በተሰጠው ጸጋና ኃላፊነት ክልል ውስጥ በራሱ መንገድ ኃላፊነቱን እንዲወጣ መፍቀድ መቻል ትልቅ ጠቀሜታ አለው። ይህ ቤተሰብ ልጆቻቸው እንደፈለጉ በራሳቸው ተሰጥኦ እንዲያድጉ ይረዳቸዋል።

3.2.5. አምባገነናዊ ውሳኔ መስጠት (*Dictatorship in decision making*):-

ይህ ስሕተት ሐዋርያዊነት በሚሰማው ባለሥልጣን/መሪ የሚከሰት ነው። ሌሎች ስሕተት እንዲሠሩ ፈጽሞ አይፈቅድም። ሰዎች የተሰጣቸውን ኃላፊነት በራሳቸው መንገድ ሠርተው እንዲያቀርቡ አይፈቅድም። እንደዚህ ያለ መሪ ትዕቢትና ኩራት

የባሕርይው መገለጫዎች ናቸው። ሐዋርያው ጴጥሮስ በመጀመሪያው መልእክቱ ምዕራፍ 5፥5 እንደጠቀሰው ለእንደዚህ ዓይነት መሪዎች ጠቋሚ ይሆናል። «---ሁላችሁ እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ። እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል።» ይህ ጥቅስ ለምን እዚያ ስፍራ እንደገባ መረዳት ባልችልም የመሪዎችን ሁኔታ የሚያውቅ ጌታ ለጥንቃቄ እንዲረዳ ብሎ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የከተተው ይመስላል። የጴጥሮስና የጳውሎስ ዘመን አልፎአል። ያ የራሱ ጥሩ ገጽታ ነበረው፤ የአሁኑ ዘመን መሪዎችም አሳቦችን በቡድን ማንሸራሸር ይጠበቅባቸዋል። ራእይ የሚመጣው ለአንድ ሰው ነው እያሉ አምባገነናዊ ስሜቶችን የሚጭኑብንን በቀላሉ ልንቀበል አይገባም። የአካል ብልት የሆኑ ሁሉ ተገጣጥመው በአንድነት ለጋራ አብረው ይሠራሉ እንጂ አይከፋፈሉም። በፈጣሪም ዘንድ አድልዎ የለም።

3.2.6. ደካማ የውክልና አሰጣጥ ማሳየት፡-

አንድ ሰው ሥራውን እንዲሠራ ከተሰጠው በኋላ፥ ያለጥፋት መልሶ የተሰጠውን የውክልና ኃላፊነት መውሰድ እጅግ አሳፋሪ ነው፤ ወይም ሥራውን እንዲሠራ ከተመደበ በኋላ ሌላ ሰው በላዩ መወከል ተገቢ አይደለም። ለምሳሌ ፡- በቤተ ክርስቲያን የሚደረግ ነገር አለ። አንድ ሰው ፕሮግራም እንዲመራ ወይም እንዲሰብክ ተመድቦ ሳለ የሰውዬውን በጎ ፈቃድ እንኳን ሳንረዳ ሌላ ሰው ይተካል። ይህ ቀላል ቢሆንም ለጊዜው ይጎዳል። መወከል ተገቢና አስፈላጊም ነው ቢባልም ውክልና ሁልጊዜ ውጤታማ ነው ማለት አይቻል ይሆናል። በውክልና እንደ አሮን ያለ ታላቅ ካህን እንኳን ሙሴ ወደ ተራራው ወደ እግዚአብሔር ዘንድ በወጣ ጊዜ በጠላቶቻቸው ፊት እንዲነወሩ ሕዝቡን ስድ ለቅቆ ለጣኦት አምልኮ ዳርጓቸዋል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ደቀ መዛሙርትን በታላቁ ተልእኮ መሠረት አምባሳደር/መልክተኛ አድርጎ ወክሎ ልኳል። (ማቴዎስ 28፥19፥ ኤፌሶን 6፥20፥ 2ኛ ቆሮንቶስ 5፥20ን ይመልከቱ)። መልእክተኛ የሚለውን የአማርኛው ትርጉም በእንግሊዘኛ አምበሳደር (Ambassador) ይለዋል። የተወከሉትም የአምባሳደርነት ተግባራቸውን በሚገባ ለመወጣታቸው ታሪክ ምስክር ነው። «በደላቸውንና ችግራቸውን ለተባበሩት መንግሥታት የሚያቀርብላቸው ተወካይ ባይኖርም፥ ተልእኮአቸውን ፈጽመው ወደ ቅድስት አገራቸው ገብተዋል።» በወቅቱ ሰብአዊ መብት ተከራካሪ የሚባል ባይኖርም፥

ለመብታቸው ሳይሆን ለሰማያዊ መንግሥትና ሕይወት (ከዚያ የሚበልጥ የለምና) ተጋድለው አልፈዋል። በአሁኑ ጊዜም በገነት በክብር እንዳሉ እርግጠኛ ነኝ። ወካዩም ጌታ ውክልናውን ሰጥቶ አልተዋቸውም። እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእነርሱ ጋር ሆኗል፤ ተግባራችንን በሚገባ የምንወጣ ከሆነ ከእኛም ጋር ይሆናል።

በአሁኑ ዘመን ያለን አማኞች የክርስቶስ አምባሳደር መሆናችንን ብናውቅ ኖሮ ዙሪያችንን የከበቡን ችግሮቻችን ሁሉ ሊቃለሉ ይችሉ ነበር ብዬ እገምታለሁ። የአገሩን መንግሥት ሥርዓት የማይጠብቅ አምባሳደር አይ ባልም፤ ዓመፀኛና ተቃዋሚ እንጂ። ለምሳሌ፦ በደረቅ ቼክ ግዢ የሚፈጽምንና በዱቤ የሚያዝ አምባሳደርን ምን ትሉታላችሁ? በመሠረቱ ውክልና የራስን ክብር ለሌላ ማጋራት ሲሆን ጌታም ያደረገው ያንኑ ነበር። የመለኮቱ ባሕርይ ተካፋዮች በተሰፋ ቃል እንድንሆን ሲያደርግ የተጸጸተበት ነገር አልነበረም፤ ወደፊትም አይኖርም። (2ኛ ጴጥሮስ 1፥4ን ይመልከቱ)።

ውክልና በራሱ ሰፊ ትምህርት ሲሆን በዚህ ክፍልም ሰፋ አድርጎ ማየት የሚያስፈልግ ይመስለኛል። መሪዎች ለምን ውክልና አይሰጡም/ ውክልና መስጠት አይፈልጉም? በተበተነው መጠይቅ ውስጥ «መሪዎች በቀላሉ ሥልጣን የሚለቁ ናቸው። እውነት/ውሸት» ለሚለው ጥያቄ [90.4%] የሚሆኑት መላሾች ውሸት ነው፤ በቀላሉ አይለቁም ብለዋል። የማይለቁበትም ምክንያት ራሳቸውን ከሌሎች የተሻሉ አድርገው ስለሚቆጥሩ፥ ርስተ ጉልት የሆነ ስለሚመስላቸው፥ ክብርና ጥቅም እንዳይቀርባቸው፥ ለሚወዱት ብቻ ስለሚያወርሱ፥ ለዘላለም የተሰጣቸው መጠሪያቸው ስለሚመስላቸውና ሙጥኝ ብለው ስለሚይዙት፥ መኖሪያቸው ስለሆነ፥ በሌሎች ስለማይተማመኑ፥ ወዘተ... የሚሉ መልሶችን ለማግኘት ተችሏል።

ከተመለሱት መጠይቆች ውስጥ 3 ሰዎች ወይም [7.1%] ብቻ እውነት ብለው መልሰዋል። ቀጥሎም ላለው ጥያቄ «መሪዎቻችን ጉዳዮችን በማከፋፈልና በውክልና ያምናሉ?» ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ [64.3%] የሚሆኑት መወከል የሚያስፈራቸው ይመስለኛል ሲሉ፥ [59.5%] ደግሞ «ግድ ካልሆነባቸው አይወክሉም» ብለዋል። [2.4%] ግለትም አንድ ሰው ብቻ «በደስታ ይወክላሉ» የሚለውን መርጧል። ይህ አሃዝ ብዙ ነገሮችን ሊያመለክት ይችላል። ታዲያ ምን ይሻላል? ምን ታዝበዋል?

በመሠረቱ መሪዎች ተግባርን ማከፋፈልና መወከል የሚፈሩበት ስድስት ነጥቦች ይኖራሉ ይባላል፦

1. ሥራውን ለሌላ ብሰጥ ሥልጣኔን አጣለሁ፥ ሥራውንም ልቀማ እችላለሁ ብሎ መፍራት (Insecurity)፥ የድርጅቱንም ይሁን የግለሰብን የአመራር ዕድገት ከድኖ ይይዘዋል፥ አፍኖ ያስቀረዋል። ይህንን መሰል አመራር ዶ/ር ማክስ ዌል (The Law of Lid)* ይሉታል። በመሆኑም የእኛ አመራር የሌላውን ዕድገት ይወስናል፤ አፍኖ ይይዘዋል፤ ወይም ይለቀዋል።

2. ሥራው በደንብ አይሠራም ብሎ መገመት/መፍራት--ያለ እኔ ሥራው አይሠራም ብሎ ማሰብ፥ የበታች ሠራተኞችን/ ታዳጊ አገልጋዮችን አለማመን ወይም በእነርሱ አለመተማመን/«ኮንፊደንስ» ማጣት። ሌላው ስሕተት እየሠራም ቢሆን ካልተለማመደ እንዴት ሊያድግ ይችላል? ስሕተት ማረም በሚቻልበት ጊዜ ቢሠራም ውድቀት አይደለም።

3. ሥራው ከእኔ በበለጠ ሁኔታ ከተሠራ በእኔ ላይ ችግር ይፈጠራል ብሎ ማሰብ፤ የበታች ሠራተኞችም ሥራውን በተሻለ መንገድ ሲሠሩት አለቃው የሚደነግጥበት ወቅት ይኖራል። ከዚያም ሁለተኛ አይወክለውም። ለውጥ ያስፈራዋል። በመሆኑም ሌላ ዓይነት አሠራር እንዳለ ለመቀበል ያዳግታቸዋል። የእነርሱ ዓይነት አሠራር ብቻ ትክክል ይመስላቸዋል።

4. በሌሎች ላይ መደገፍን መፍራት፥ እኔ ብቻዬን እወጣዋለሁ ብሎ መገመት ትልቅ ስሕተት ነው። አንዱ ለሌላው ያስፈልጋልና። 50 ሎሚ ለአንድ ሰው ሸከሙ፥ ለ50 ሰዎች ግን ጌጣቸው ነው ይባልስ የለ?

5. አንዳንዱ ደግሞ በማሠልጠን አለማመንና ጊዜውን የሚያባክን ስለሚመስለው አይወክልም።

---

* Dr. John C, Maxwell, The 21 Irrefutable Laws of Leadership, Video # 1, 1998.

6. ሥራውን ከመጠን በላይ መውደድና ለሌላ ለመስጠት መሰሰት ሲሆን ሌሎችም ነጥቦች ሊኖሩ ይችላሉ።

ይህንና መሰል ችግሮችን በመፍራት መሪዎች የበታቾቻቸውን ላይወክሉ ይችላሉ። በእርግጥ ውክልና ሲሰጥ ኃላፊነትንና ሥልጣንን ነው እንጂ ምንጊዜም ተጠያቂነትን በሙሉ መወከል አይቻልም። ተጠያቂነትን ለመወከል ማሰብ መወከል(Delegation) ሳይሆን፥ ተጠያቂነትን ማውረድና ከደሙ ንጹሕ ነኝ ማለት (Abdication) ይባላል። ሁል ጊዜ ያስጠይቃል። በአሜሪካ የኤስ. አይ. ኤም. ዓለም አቀፍ አማካሪ የሆኑት ሚ/ር ሌሪ ዲክ* እንደሚሉት «---ውክልና በሌሎች ሰዎች ውስጥ የራስን ተግባር ማከናወን» ማለት ነው። በሌሎች ሰዎች እኛ ልንደርስበት የማንችለውን መድረስ ማለትም ነው።

ሆኖም ግን ውክልና የሚደረገው ሁልጊዜ ከላይ ወደ ታች ሆኖ፥ ኃላፊው ማለትም መሪው ከመወከሉ በፊት በቅድሚያ ሊገነዘባቸው የሚገቡ ነጥቦች ይኖራሉ። እነዚህም፥-

- ከሰዎች መካከል ብቁ ሰው ወይም ለማደግ ተስፋ ያለውን ሰው መምረጥ፥ እርሱንም ማሳደግ፥

- በሰውዬው ደግሞ መተማመንን (Confidence)ማሳየት፥

- ኃላፊነታቸውንና ሥልጣናቸውን ግልጽ ማድረግና ገደባቸውም እስከ ምን ድረስ መሆኑን መወሰንና፥ ማሳወቅ፥

- ሥራው እንዴት መሠራት እንዳለበት ተጽዕኖና ጫና አለማድረግ፤ በምንም ዓይነት አድርጎ ይሥራው ፍቀዱለት፥ ሞክሩት፥ ከነተረቱ «የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው» ይባል የለም? በፈለገው መንገድ ይሥራው ብቻ ውጤት ያስገኝ። ቢወድቅም/ለጊዜው ባይሆንለትም ክፍተት ሊሰጠው ይገባል። ማንም ሰው በእናቱ ሆድ ተምሮ የወጣ የለምና። መውደቅም ለዘላለም አለመነሣት ማለት አይደለም። አስተዋይ ሰው ከውድቀቱ ብዙ ነገር ሊማር ይችላል። ይህ ማለት ግን ከድርጅቱ ዓላማና ግብ ውጪ እንደፈለገ ያድርግ ማለት ላይሆን ይችላል።

- በእርሱ ዓውደ ክልል ተጠያቂነት እንዳለበትም ማስገንዘብ። ስለሆነም ክትትልና/ቁጥጥር ማድረግ አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ ይኖራል ማለት ነው።

---

* Larry Dick, *Unpublished Materials on Leadership*, (USA, 1997).

– በመጨረሻም ተግባሩን ሲፈጽም ምስጋናና አክብሮት መስጠት። ስላደረገው ወይም ስለፈጸመው ተግባር በሰው ፊት ሊመሰገን ይገባዋል። ይህ ባህላችን ባይሆንም መመስገንን ማንም አይጠላም። የሚጎዳ ነገር ባለመሆኑ ልንለምደው የሚያስፈልግ አዎንታዊ ባህል ነው።

ሌላው «አፈር ድሜ በልቶ» በሠራው ዕድገት ያገኙ አለቆችና ሹመት ያገኙ መሪዎች አውቃለሁ። ያን ሰው ግን ዘወርም ብለው አያመሰግኑትም። *«---ጠቢብ ድሀ ሰውም ተገንባት፥ ያችንም ከተማ በጥበቡ አዳናት፤ ያን ድሀ ሰው ግን ማንም አላሰበውም»* (መክብብ 9፥14-15ን ይመልከቱ)።

ስለዚህ ስንወክል የሚከተሉት አምስት ነጥቦች ትኩረት ሊቸራቸው ይገባል፦

1. ውክልናው በአመኔታ ላይ ተመሥርቶ በውጤት የሚታይ እንጂ «እንደዚህና እንደዚያ ሥራው» መባል የለበትም።
2. ኃላፊነቱ በትክክል ገብቶት መወከሉን ማረጋገጥ።
3. የኃላፊነትና የሥልጣን ገደቡን/ ወሰኑን በትክክል ማስቀመጥ።
4. ሊሠሩ በሚገባቸው ደረጃዎች (Standards) እና ክልልሎች ስምምነት ላይ መድረስ፤ የሥራ ግብዓቱንም ማረጋገጥ።
5. ተግባሩን ሲያከናውን በአግባቡ ለመፈጸሙ ቁጥጥርና ክትትል እንደሚደረግበት ማሳወቅ። እንደዚህ ዓይነት ክትትልም ተወካዩን ለማሳደግና በበለጠ ሙያውን እንዲያዳብር እንጂ እንደ ወንጀለኛ መረጃ ሰብስቦ ለማጥቃት አለመሆኑን መግለጽ። ቁጥጥሮች በመሠረቱ ለማስተማር እንጂ ለመወንጀያ መሆን የለባቸውም። ቁጥጥር ለማስተካከያ፥ ለማረሚያና ለማቅኛ ካልሆነ ጎጂ ነው።

በአጠቃላይ ውክልናን መለማመድና በቡድን ተግባርን ማከናወን የተሻለ ልምድ ነው። በቡድን የተሠራ ተግባር የተሻለ እንደሚሆን አያጠራጥርም። ከአትሌቶቻችን ይህን መማር የሚቻል ይመስለኛል። ክፍል ሦስት ውስጥ በቡድን አሠራር ላይ ሰፋ ያለ መግለጫና ማብራሪያ ቀርቧል።

3.2.7 የመግባባት ችግር (Communication Chaos) እና የግንኙነት አለመስመር፦

የግንኙነት አስፈላጊነት በማናቸውም ደረጃ (በግለሰብም ይሁን በቢሮ) የሚጠበቅ ነው። በዓለም ላይ ሰው የተፈጠረው ግንኙነት እንዲለማመድ ይመስላል። ግንኙነት ካልሰመረ በቤተሰብ መካከል እንኳን ከፍተኛ ቀውስ ይከተላል። ባልና ሚስት መግባባት ከሌላቸው ትዳራቸው ትርምስና መለስተኛ የጦር ሜዳ ይሆናል። ልጆችና ወላጆችም እንደዚሁ ግንኙነት ያስፈልጋቸዋል። በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ የቤተሰብ መበላሸትና መፍረስ ትልቁ ምክንያትና ችግር የግንኙነት እጥረት ነው። በሥራ ዓለምም በቢሮ ውስጥም ሆነ በውጭ ግንኙነት ያስፈልጋል። በተለይ በሥራ ዓለም በማንኛውም ደረጃ ይሁን ግንኙነት ወሳኝ ነው።

በዚህም ግልጽ መሆን ያለበት፡-

- ራእይና የድርጅቱ ወይም የቡድኑ የአመለካከት እሴት።

- የእዝ ሰንሰለትና የሥልጣን ተዋረድ፡- ለምሳሌ፡- ማን ምን መሥራት እንዳለበት፥ ማን ለማን ተጠሪ እንደሚሆን፥ ወዘተ... መገለጽ አለበት።

- ድርጅታዊ መዋቅር፡- ይህ እንዲያውም የሰዎች የተግባር ካርታ ነው ይባላል። የሥልጣን ተዋረድን በዚህ ሁኔታ ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

- የሥራ መዘርዝር፡- የኃላፊነትና የግዴታዎች ዝርዝር በትክክል መቀመጥ ይገባዋል። በመጨረሻም እንዴት እንደተሠራ የሥራ ዘገባ ማቅረብንም ይጨምራል።

ታዋቂው መንፈሳዊ ሰው ፍራንሲስ ሼፈር አንድ ጊዜ እንደዚህ ብሎ ነበር። «በእግዚአብሔር መንግሥት ትንሽ ሕዝብና ትንሽ ቦታ የለም»። ስለዚህ በሁሉም ደረጃ ያሉ ሠራተኞች ግልጽ መመሪያ ያስፈልጋቸዋል። ይህ ለሁሉም የሚታወቅ፥ ግልጽ የሆነና ትክክለኛነቱም የተፈተነ መሆን ይገባዋል።

ሁልጊዜ አንድን ነገር ስንናገር ሰሚው የሚሰማው በግሉ አእምሮ መስተካከል (Mindset) ሲሆን፥ ተናጋሪው ለምን አልገባውም ብሎ መናገር ባይኖርበት መልካም ይሆናል። ሰሚው ከሌላው ሰው የተነገረውን መልእክት በራሱ አስተሳሰብና የትርጉም ክፍል ውስጥ አሳልፎ እንደተረዳው ነው የሚሰማው። ስለሆነም የአንድ ነገር ትርጉም ያለው በሰውዬው በራሱ ውስጥ እንጂ በተናጋሪው ቃል ውስጥ እንዳልሆነ የቋንቋ አዋቂዎች ያስረዳሉ።

ግንኙነት የጋራ መግባባትን ሲጠይቅ መቼ መናገር እንዳለብን (ጊዜን)፥ ማን መናገር እንዳለበት (ባለቤትን)፥ የት መናገር እንዳለበት (ቦታን)፥ ምን መናገር እንዳለብን (ይዘትን)፥ ለምን መናገር እንዳለብን (ምክንያትን)፥ እንዴት መናገር እንዳለብን (ዘዴና ስልትን) ማወቅ ይጠይቃል።

ለምሳሌ፡– በ 1ኛቆሮንቶስ 11፥27 ውስጥ ብዙዎቻችን በትክክል የማናነበው ቃል አለ። ይኸውም «ሳይገባው» የሚለው ቃል *(understanding)* ሲሆን፥ *(Worthy)* ከሚለው ጋር የነላ ልዩነት እንዳለው ማየት ይቻላል። ሳይገባው ማለት ነገሩን በትክክል ሳይረዳው ማለት ነው። ትክክለኛ እዚህ ቦታ የተጠቀሰው ስንኝ ግን «ሳይገባው» ማለትም ለነገሩ ብቁ ሳይሆን/ነገሩን ሳይመጥን ማለት ነው። ስለዚህ በቅዱስ ቁርባን ወቅት ይህ ጥቅስ ሲነበብ ሁለቱንም አድርጎ ማንበብ ስሕተት ነው። እንደዚህ አድርገው የሚያነቡ ብዙ ጊዜ አጋጥመውኛል። ነገሩ ቀላል ቢመስልም በሌላው ትርጉምም እንደዚሁ ቢደረግ ሥነ መለኮታዊ ችግር ያስከትላል።

ግንኙነትን በሚመለከት አንድ ምሳሌ መጨመር ጥሩ ነው። አንድ ጊዜ በአንድ የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ውስጥ ቤት እንዲያጸዱ ለልጆቹ መመሪያ ተሰጣቸው ይባላል። ልጆቹ የመጡት ከተለያየ ቦታ ስለ ነበር ኃላፊው እምብዛም አያውቃቸውም። አብዛኞቹ ልጆች የመጡት ከክፍለ ሀገር ነበርና የሚጸዳ ነገር ሁሉ በውኃ መጽዳት እንዳለበት ያውቃሉ። በመሆኑም ቤቱን በማጽዳት ላይ ሳሉ አንደኛው ልጅ በጣም ጮሌ ስለነበር መልካም ያደረገ መስሎት ቴሌቪዥኑን በውኃና በእሞ አጠበው። ለዚህ ሁኔታ ጥፋተኛው ማን ነው? ትእዛዝ አስተላላፊው ወይስ ትእዛዝ ተቀባዩ? ትእዛዝ አስተላላፊው ነገሩን በትክክል መረዳታቸውን የመገንዘብ ኃላፊነት አልነበረበትም ወይ? የገጠር ልጆች ስለ ቴሌቪዥን ምን ያውቃሉ? በእርግጥ የዚህ ዓይነት ነገር ሌላም ችግር ሊያስከትል ይችላል።

ግንኙነት በአንድ በኩል/በአንድ መንገድ *(one way)* ብቻ ሲሆን ሁልጊዜ ውጤቱ አሳዛኝና የማያረካ ይሆናል። ነገሩ እንዴት ይሆናል ብሎ መጠየቅ ይቻል ይሆናል። ግን ይሆናል። የሁሉም ሰው የመረዳት ችሎታ አንድ ዓይነት አይደለም። ሁሉ በገባውና በደረሰበት ሊመላለስ ሚዛናዊ ኑሮ መኖር ይቻል ይሆናል። (ፊልጵስዮስ 3፥16ን ይመልከቱ)።

ከዚህ በተረፈ በግንኙነት ወቅት መስማት ብቻ ሳይሆን ማዳመጥ *(Listening)* በጣም አስፈላጊ ነው። አንድ መሪ ማዳመጥ መቻል አለበት። የመሪ ትልቁ ችግር ግን አለማዳመጥ ነው።

አንዳንድ መሪ ደግሞ እርሱ ሳይሰማና ሳያዳምጥ ሌላ እንዲሰማለትና እንዲያዳምጥለት ጆሮ ይፈጥራል። ይህ እንግዲህ ትልቅ ስሕተት ነው። ትልቁን እንደሚሰማ ትንሹንም በእኩል ደረጃ መስማት ይገባዋል። ሊያዳምጥ ይችል ይሆናል፤ በትክክል መስማትንና ቁም ነገርን መረዳትና መለየት በጣም ወሳኝ ነው። የበታች ሠራተኞች ሊናገሩ ወረቀት ማገላበጥ፥ ፋይል መነካካት፥ አጀንዳ ማንሣት፥ «ሂድልኝ ልሰማህ እልፈልግም ወይም ጊዜ የለኝም» እንደ ማለት ነው።

ዶ/ር አንቶኒ ዲሉዛ እንደሚሉት ሰዎች 45 በመቶ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በማዳመጥ፥ 30 በመቶውን በመሰማት፥ 16 በመቶውን በማንበብና 9 በመቶውን በመጻፍ ነው ይባላል። ይህ በእርግጥ ምን ያህል ትክክለኛ መሆኑ በእኛ ሀገር በጥናት አልተረጋገጠም ይሆናል። በተለይ በከተሞች አካባቢ ከዚህ እንደማይለይ እገምታለሁ። ትንሽም የምጠራጠረው ማንበብና መጻፍ ላይ ብቻ ነው። በተለይ የማንበብን ባህል ማዳበር እጅግ ጠቃሚ ነው። ስናዳምጥም ለውጤት ማዳመጥ መልካም ነው። ነገርን ለመረዳት፥ ተረድቶም መፍትሔውን ለማግኘት ማዳመጥ ይበጃል።

ለማዳመጥ የሚከተሉትን አራት ነጥቦች መገንዘብ ይጠቅማል፦

1. ፈቃድ መኖር አለበት፦ እስቲ ልስማው፥ ጊዜ ልስጠው ማለትን ይጠይቃል።
2. ሰውን ማክበርና ቦታ መስጠት (value) ይጠይቃል። የሰውን ልጅ ክቡርነት መረዳትና ማንም ቢሆን አጋጣሚ ቢያገኝ እንደ እኔ ሊሆን፥ ሊሠራ፥ ሊወጣና ሊገባ፥ ወዘተ... እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል። ማንም በወንድሙ ላይ ሊኮራና ሊዘናና አይገባውም። (ዘዳግም 17፥19-20ን ይመልከቱ)።
3. ፍቅር ይጠይቃል፦ ሰውን በአርአያ ሥላሴ በመፈጠሩ ብቻ እንኳን ርኅራኄና ፍቅር ማሳየት ይገባል።
4. ችግሩን ደግሞ ለመካፈል ወይም ለማቃለል ውሳኔ ማድረግን ይጠይቃል።

በአጠቃላይ እንግዲህ ማዳመጥ በልብ ሲሆን መስማት በጆሮ ነው፤ በእርግጥ ስንሰማ አጥርተንና ምርቱን ከግርዱ ለይተን መስማት ይኖርብን ይሆናል። ሆኖም መስማት፥ ማዳመጥ፥ አሁንም ማዳመጥ እጅግ አስፈላጊ ነው። አንዳንድ ሰዎች ቴሌቪዥን ፊት ይቀመጡና ይሰማሉ፤ ግን አያዳምጡም። «የቅድሙ ዜና አንባቢ ምን ማለቱ ነው?» ብላችሁ ብትጠይቋቸው «እንጃ! ሌላ ነገር እያሰብኩ ነበር»

ብለው ሊመልሱ ይችላሉ። በትክክል ማዳመጥ በተለይ ለመሪ ጊዜ ማጥፋትን ይቆጥብለታል። ለእስራኤል ሕዝብም የተባለው ይህ ነበር፤ «---ፊት አይተህም አታድላ» (ዘዳግም 16፥19ን ይመልከቱ)።

3.2.8. የድርጅቱን አጠቃላይ የአሠራር ባህል አለመረዳት፡-

ይህም ስሕተት ብዙ መሪዎችን ለችግር የዳረገ ነው። በማንኛውም ድርጅትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ያለው የአሠራር ልምድ ምን ይመስላል ብሎ መገምገም መልካም ነው። አመለካከታችን ከሥነ መለኮት እውቀታችን መለየት ይኖርበታል።

አዲስ የተቀጠረ ሰው ለውጥ ለማምጣት ፍላጎት ሊኖረው ይችላል። ሆኖም ከሳሩም ከቅጠሉም እየተጣላና እየተጋጨ ራሱን እንዳይጎዳ በቅድሚያ የድርጅቱን የአሠራር ባህል በጥሞና ቢረዳ ይጠቀማል። በጎላም መታረም፥ መሻሻልና መለወጥ ያለበትን በውል ለይቶ ሊያውቅ ይችላል። ሁል ጊዜ አፍርሶ መሥራት ላያስፈልግ ይችላል። ግማሹ ጥገና፥ ግማሹ ድፍረት፥ ሌላው ኃላፊነት የሚወስድ መሪ ይሆናል የሚጠይቀው። ምናልባት የሚያስፈልገው መጠነኛ እርምት ይሆናል። ይህን ባለመረዳትና ሌላው በፊት በሄደበት አልሄድም፤ በጻፈበት አልጽፍም፤ ወዘተ... ካልን ከሰዎች ይልቅ ምስኪኖች ልንሆን እንችላለን።

ይህ መሰል ተግባር የሚያመጣውን ስንከሳር ባለመረዳት መሪዎች ለችግር ይጋለጣሉ። ገና ሲጀምሩ ተቃውሞ ይጠብቃቸዋል። ስንዝር ያህልም መራመድ ያዳግታቸዋል። አንድ ጊዜ በአንድ የንግድ ድርጅት ውስጥ ስሠራ አዲስ ኃላፊ ተመድቦ መጣ።ቦታው የሚማርክ /ከገቢና ገንዘብ አንጻር/ ነበርና ሰውዬው ቦታ አልበቃ አለው። ሁሉም ውስጥ ልግባ፥ አድራጊ - ፈጣሪ ልሁን ማለትም አበዛ። ሌሎቹን አላስበላ አለ። ያኔ ዓይንህ ለአፈር ተባለ። ዋና ሥራ አስኪያጁም የዋዛ አልነበሩምና ዝም አሉት። ከሁሉ እየሄደ መላተም አበዛ። በድርጅቱ ውስጥ ያለሁት እኔ ብቻ ነኝ ለማለት የቃጣው ይመስል ነበር። በጎላም ራሱን ጎድቶ የአንድ ወር ደመወዙን እንኳን ሳይበላ በድንገት ሞተ። ባይሞት ኖሮ ምን እንደሚሆን እግዚአብሔር ይወቅ።

በድርጅቶችም በሌላም ቦታ አልፎ አልፎ እንደዚህ ያሉ መሪዎች ይኖራሉ። ይህ በእርግጥ የሥነ አእምሮና የሥነ ባሕርይ ችግር ይመስላል። ያለ እነርሱ አዋቂ፥ ያለ እነርሱ አስተዋይ፥ ብርቱና ታታሪ ሠራተኛ የሌለ ይመስላቸዋል። እንደዚህ ዓይነት የአመራር

ስልት ያላቸው ሰዎች ደንበኛ የ "ሄ" ቲዎሪ/ንድፈ አሳብ አራማጆች ናቸው። ይህ ጽንሰ አሳብ ለሰው ልጆች ቦታ የሌለው፥ ሁል ጊዜ ጎትጓችና አነሣሽ ያስፈልጋቸዋል የሚል ነው። ከራሳቸው ማንነት በስተቀር የሚታያቸው ነገር የለም። «እበላለሁ ብሎ መበላት ይመጣልና» ነገርን ሁሉ በእርጋታና በሰከነ ዘዴ ማከናወን እጅግ ጠቃሚ ነው። በተለይ ከመንፈሳዊ መሪዎች ይህ ፈጽሞ አይጠበቅም። ጌታም እንደዚህ አላስተማረንም።

ለምሳሌ፡- በአንድ ወቅት አንድ የምቀርባቸው «የትልቅ ቤተሰብ» ወገን የሆኑ እናት ዳገት/ፎቅ ሲወጡና በአንድ ጉዳይ ሲበሳጩ ተመልክቼ፥ «ችግር ነው ጌትነት» አልኳቸው። ለካስ እርሳቸውም የዋዛ አልነበሩም «ካላወቁበት» ብለው መለሱልኝ። ይህ ብዙ ዓመታት አስቆጥሯል፤ ዳሩ ግን አልረሳውም። እውነትም ሁሉም ነገር ችግር የሚሆነው ካላወቁበት ብቻ ነው። ብናውቅበትማ ልንጠቀምበት እንችላለን። በድርጅት ውስጥ ትንሹም ቢሆን ትልቁ ሁሉም ድርሻ አለው። የጽዳት ሠራተኛ እንኳን ቢሮ ካላጸዳች መግባት ይከተላል። እስቲ ለአንድ ሳምንት ቢሮዎን ሳያጸዱ ይቆዩና ይህን ሁኔታ ለማረጋገጥ ይሞክሩ።

3.2.9. ተተኪ ሳይኖር/ሳያፈራ ውጤታማ ለመሆን መፈለግ፡-

ተተኪ የማያፈራ መሪ እንደ ወደቀ ዛፍ ይቆጠራል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሙሴ ኢያሱን፥ ኤልያስም ኤልሳዕን፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ደቀ መዛሙርትን ከዚያም በዘመናት ውስጥ ያሉትን መሪዎች አፍርተዋል። ጳውሎስም ጢሞቴዎስንና ቲቶን ሌሎችንም አፍርቷል። ኢያሱንና ኤልሳዕን ስንመለከት ግን ተተኪ ያላፈሩ መሪዎች ነበሩ ማለት ይቻላል። በመሆኑም ነው እነርሱ ተልእኮአቸውን ሲጨርሱ ሕዝቡ በቀጥታ ወደ ችግር ውስጥ የገባው። ራእይ የሌለውና ሁልጊዜ በሌሎች ላይ የሚደገፍ መሪ ሌሎችን ሳይተካ ሥራውን በትኖ ያልፋል።

ሁልጊዜ ተተኪ ማፍራት የጥሩ መሪ ባሕርይ ነው። ጥሩ መሪ ራሱን በሌላ ይተካል። በእርጅና ወቅት ወዘናውን እስኪጨርስ፥ እስኪሟጠጥና ለዛ ቢስ እስኪሆን ድረስ መጠበቅ አይኖርበትም። መሪ መጀመር ይችላል። መጨረስ ግን ሌላ ጉዳይ ነው። በተለይ በጥሩ አጨራረስ መጨርስ ውብ ነው/ ክብርም ነው። በዘመን ሁሉ አገልግሎ ማለፍ ምንኛ መታደል ነው?

በአገራችን ያሉ መሪዎች ሳይመሰገኑ ከመንበራቸው የሚባረሩበት ምክንያቱ ምን ይሆን? ሁልጊዜ ከወንበራቸው ለመልቀቅ ባለመፈለጋቸው ገፍቶ የሚጥላቸው እስኪመጣ ድረስ ይጠብቃሉ። እነርሱ እንዳደረጉ በተራቸው ይደረግባቸዋል። ጠመንጃም ሁልጊዜ ሌላ ጠመንጃ ያስከትላል፤ መግፋትም መገፋትን ያመጣል። «እረ በእውነቱ ችግራችን ምን ይሆን?» የዕድር አለቃም ቢሆን ከሥልጣኑ (ይህም ቢሆን ሥልጣን ከሆነ ማለት ነው) ከወረደ በቃ ዕድሩ አለቀለት ይላል፤ እርሱ ስለሌለ ይፈርሳል ብሎ ይገምታል። ከእርሱ የተሻሉ ሰዎች ቢመጡም ሳያደንቃቸው እንደተቻቸው ይሞታል፡ መገልበጥ አልሳካ ካለው ማለት ነው።

የአገራችን ችግር በእርግጥ ሀቀኛ መሪዎች ተገናኝተው ቢወያዩ፡ ከራሳቸው ምቹ ክልል (Comfort Zone) ቢወጡና የፖለቲካ ዓላማቸውንና መመሪያቸውን ከሕዝብ ችግርና ፍላጎት በላይ ባያደርጉ፡ በቀላሉ ሊቀረፍ ይችል ነበር የሚል ግምት አለኝ። ችግራችን እንዳይቃለል የምናደርገው እኛው ራሳችን ነን። የራሳችንን ጥፋት ስለማናምን፡ ሁል ጊዜ ሌላ ሦስተኛ ሰው ላይ ማሳበብ ስለሚቀለን፡ «እነዚያ ናቸው፡ እነዚህ ናቸው፤ ስለማይወዱን ነው፤ ቀንተው ነው፤ ሀገራችንን ለመውረር ነው፤ ሕዝባችንን ለማታለል ነው፤ ወዘተ...» እያልን የሆነ ያልሆነ ነጥብ እየደረደርን ችግሩን እናባብሳለን። እፍረት ሳይሆን የጥፋተኝነት ስሜት ተሰምቶን አንድ እርምጃ ወደፊት ብንሄድ ለሀገርና ለወገን ምንኛ በጠቀምን ነበር?

ስለዚህ ተተኪ የማፍራት ጥበብ በዘመኑ አባባል አስተማሪና መካሪ (Mentor) ይባላል። ለምሳሌ ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ተግባሩን እንዲወጣ ያበረታውና ያጸናው ይደግፈውም ነበር። ሙሴም ለኢያሱ ይህንኑ ያደርግ ነበር። በእርግጥ እንደዚህ ዓይነት መካሪና ደጋፊ (Mentor) ማግኘት ቀላል አይደለም። እግዚአብሔር ሲሰጥ ብቻ የሚገኝ ነው። እንደዚህ ያለ ሰው ከበታቹ ያለውን ሰው እንደ አጋሩ እየተመለከተው ይንከባከበዋል፤ ይመክረዋል፤ ያበረታታዋል። ሲሳሳት ያስተካክለዋል፤ ሲወድቅ ያነሣዋል፤ ሲያዝን ያጽናናዋል፤ ሲደሰት አብሮ ደስ ይለዋል። በሕይወቱ እድገት እንዲያሳይ ይጥራል። ይህ እንግዲህ መሰጠት ነው የሚባለው።

3.2.10. ለሚሆነው ነገር ሁሉ ትኩረት አለመስጠት፡-

አይደርስም የተባለ ነገር ሊደርስ ይችላል። አይመጣም የተባለውም ይመጣል። በመሆኑም ራስን ለሁሉ ነገር ማዘጋጀት ይጠቅማል። መሪ የወደፊቱንም ነገር ቢሆን በአእምሮ ሥሎ በአንክሮ መመልከት ይጠበቅበታል። ለድርጅትም ቢሆን ለቤተ

ክርስቲያን መሪዎች ራእይ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል። ስለዚህ ነው የአፍሪቃ መሪዎች በአሁኑ ላይ ብቻ ሲያተኩሩና ሲተረማመሱ የወደፊቱን ትውልድ የማያስታውሱት። በዚህም ራእይ የለንም ይባላል።

ራእይ ያለው መሪ ከዛሬ ዓመትና ከዚያም በኋላ ድርጅቱ ወይም ቤተ ክርስቲያኑ እዚህና እዚያ ሊደርሱ እንደሚችሉ ያስባል። በእርግጥ አንድ ሰው ራእይ አለኝ ስላለ ብቻ መሪ ይሆናል ማለት አይቻልም። ራእይ ያለው በአሰበውም ዘዴ እዚያ ለመድረስ ይሠራል፤ ያሠራል፤ ያስተባብራል፤ ያሰልፋል። ብቻውን ቢሮጥ ብቻውን ያሸንፋል፥ ወይም ይሸነፋል። ደስታውንና ድሉን የሚጋራው፥ የሚያደንቅለት አይኖርም። ራሱ ለራሱ ያጨበጭባል። በዚህም ደስታው ፍጹም ሊሆንለት አይችልም፤ ምናልባትም ደስ ቢለው ማለት ነው። አትሌቶቻችን ብቻቸውን የሮጡ አይመስልም፤ ሕዝቡ አብሯቸው የሮጠና ሽልማቱን የተቀበለ ያህል ነው ደስታው የነበረው። ከደስታ ብዛት የሕይወት መሥዋዕትነት እንኳ ተከፍሏል። ሕዝቡ ደስ ብሎት የማያውቀውን ያህል አስደስተውታል። ድሉና ደስታችን የጋራ በመሆኑ ለወገን መኩሪያና አለኝታ ሆነዋል ማለት ይቻላል። በተለይ ከአገር ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ምን እንደሚሰማቸው መገመት አያዳግትም። የምንበላውና ሀብታችን ሳይሆን ልምምድ ከዓላማ ጽናት ጋር ሲገናኝ የት እንደሚያደርስ መገመት ይቻላል።

መሪ ራእይ በመቅረጽ ሊደርስበት ያለውን ስፍራ ከአድማስ ባሻገር መቃኘት ይኖርበታል። መሪ ሌሎች ሳያዩ እርሱ አስቀድሞ የሚያይ ነው። ምኞትና ስሜት ሁሉ ግን እንደ ራእይ አይቆጠርም። በመሠረቱ እዚያም ለመድረስ ተከታዮቹ፥ ደጋፊዎቹ፥ የሥራ ባልደረቦቹ፥ ወዘተ... በቅርብ እንዲከተሉት ያስፈልጉታል። አለበለዚያ ግን አይሳካለትም።

ለምሳሌ፡- ራእይ የሚለው ቃል፥

ራ :-ራቅ ያለ አመለካከትን ያመለክታል እንበል

እ :-ደግሞ መሪው የሚኖረውን ዕይታ ሲያስገነዝብ

ይ :- ይጠይቃል ብለን ብንወስደው፥ ራእይ በአጠቃላይ ራቅ ያለ ቦታ ለመድረስና ውጤታማ ለመሆን ዓላማ ካለህ አተኩረህ ዕይ ተብሎ ሊፈታ ይችላል።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው፥ «ራእይ ባይኖር ሕዝብ መረን ይሆናል» (ምሳሌ 29፡18)። አንድ መሪ ራቅ ያለ ዕይታ ያስፈልገዋል። ራእይ ድርጅታዊ ሕልም/ቅዥት አይደለም። ሕልም ግልጽ አይደለምና። ራእይ ግን እንዲፈጸም ግልጽ መሆን ይገባዋል። በሀገራችን አንድ ትልቅ መሪ ማታ የታየውን ሕልም ጥዋት ፈጽሙ እያለ ባለሥልጣናትን ያስቸግር ነበር ይባላል። ናቡከደናፆርም ይህንኑ ነበር ያደረገው። በእርግጥ አምባገነኖች ይኸው ናቸው። መሪ ቁጥጥር (Supervision) የሚያደርግ ከሆነ ዕይታው ከሌሎች የላቀ ሊሆን ይገባዋል። የእንግሊዘኛው ቃል የሚያመለክተው ዕይታው (Vision) የላቀ (Super) ሰው መሆኑን ነው። በመሆኑም መሪ ለሚሆነው ነገር ትኩረት ሊሰጥ ይገባል። ዕይታው ከሌሎች የላቀ እንዲሆን ይጠበቃል።

3.2.11. ችግርን ከማቃለል ይልቅ ማባባስ፡-

ችግሮች እንዲጠነዙ ማድረግ፥ እርሾ ገብቶባቸው እንዲኮመጥጡ ማቆየት እጅግ የከፋ ነገር ነው። በወቅቱ ለመፍታት መሞከር ግን ማስተዋል ነው። አንዳንድ መሪዎች ላይ ችግሮች ይገናኙ። እንደዚህ ያሉ መሪዎች በእርጋታ በመቀመጥ ለችግሩ ሳይንበረከኩ ግልጽና በሚዳሰስ መልኩ ለመፍታት መጣር ተገቢ ነው። ምክንያቱም ጥናቶች እንደሚጠቁሙት አብዛኛው የሥራ ኃላፊ/መሪ ጊዜውን የሚያባክነው ችግር በመፍታት (Crisis Management) ነው ይባላል። የተበተኑት መጠይቆችም ይህንን አረጋግጠዋል። አስቀድሞ ችግር እንዳይመጣ መጠንቀቅ ግን ባህላችን ባለመሆኑ ሁልጊዜ በችግር እንጎዳለን። በቲዎሪ «አር» ሥራ አመራር መሠረት ችግርን ለመፍታት መሸሽ መፍትሔ አይደለም። መጋፈጥ ግን አንዱ ዘዴ ነው።

በሰዎችና በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛ የሆነውን ነገር ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው። ጳውሎስ እንዳለው፥ *«---በጌታ ፊት ብቻ ያይደለ ነገር ግን በሰው ፊት ደግሞ መልካም የሆነውን እናስባለን።»* (2ኛ ቆሮንቶስ 8፡21ን ይመልከቱ)። አንዳንዴ እግዚአብሔር ያውቀኛል፤ ምን አድርጌአለሁ? እንላለን። አድርገን ሊሆንም፥ ላይሆንም ይችላል። ሆኖም ግን በሰው ፊት በጎ የሆነውን ማድረግ መልካም ነው። ስለዚህ ሥራን በእርቅና (Reconciliation) በእርስ-በርስ ግንኙነት (Relationship) መምራት ይጠቅማል። ዕርቅም የአንድ ወገን ብቻ እርምጃ ሳይሆን የሁለቱም ታራቂዎች

የጋራ ውሳኔና ፍላጎት ሲሆን ነው ግቡን የሚመታው። ፖለቲከኞች በዚህ ላይስማሙ ይችላሉ።

ችግሮችን ለመፍታትና የዕርቅ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የሚከትሉት ነጥቦች ትኩረት ሊቸራቸው ያስፈልጋል።

3.2.11.1. ችግሩን በውል ማጤንና መገንዘብ፤ ተገንዝቦም ምን እንደሆነ በግልጽ መለየት።

3.2.11.2. የችግሩ መነሻ ምን እንደሆነ? ማን እንደ ጀመረው? እንዴት እንደ ጀመረ? ለምን እንደ ጀመረ? መቼ እንደ ጀመረ? የት እንደ ጀመረ? በውል መለየት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

3.2.11.3. ያሉትን የመፍትሔ አማራጭ አሳቦች መለየት፥ ዕቅድ ማውጣትና ችግሩን ለመፍታት መሞከር።

3.2.11.4. የሌሎች ባለሙያዎችን ምክርና ዕርዳታ መጠየቅ አስፈላጊ ሲሆን መጠየቅ።

3.2.11.5. የተሰጠውን ውሳኔና የመፍትሔ አሳብ መከታተልና ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ።

3.2.11.6. ውሳኔውን/የመፍትሔ አሳቡን የተቀበለውን ወገን ማመስገንና ማበረታታት፥ በዚያም ጸንቶ እንዲቆም እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

3.2.12. መሪዎች ራሳቸውን ከሌሎች መለየትና እርስ በርስ አለመቀባበል፦

የመሪ መደብ ያለ ይመስል ራስን እንደ ሌላ ሰው ማየትና መለየት ችግር ውስጥ ይከታል። በህገራችን አባባል ቀባሪም ያሳጣል። ስለዚህ መሪዎች ቢቻል ከሕዝቡ ጋር መቀላቀልና መደባለቅ ይኖርባቸዋል። በእርግጥ ይህ ባህላችን ስላልሆነ መቀላቀል ይከብድ ይሆናል። ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር ሲበላና ሲጠጣ አልከበደውም። አገልጋይ መሪ ገዢነት ስሜት ካልተጠናወተው ሊከብደው አይችልም። የገዢነት ስሜት፥ የባለሥልጣንነት ስሜትና የበላይነት አመለካከት የሚሰማን ከሆነ ግን ለመቀላቀልና ለመደባለቅ አስቸጋሪ ይሆንብናል።

ሰው በመሠረቱ ብቻውን እንዲኖር የተፈጠረ ፍጥረት አይደለም። አንዳንዱ አንዳንድ መሪዎች በድርጅቶችና በሚሠሩበት መሥሪያ ቤት ያላቸውን ሥልጣንና ኃላፊነት ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አምጥተው ባለሥልጣን ሊሆኑ ይመኛሉ። በሥራ ቦታ ሥልጣን አለው ማለት በመንፈሳዊ አመራሩ ሥልጣን ሊያሰጠው አይችልም። ይህ ሊሆን አይችልም። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ በመሥሪያ ቤት ሥራ አስኪያጅ ከሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ትንታኔ፥ እውቀትና አፈታት መንፈሳዊ ሥልጣን እንዳለው ባለሥልጣን (Authority figure) ናቸው ማለት አይቻልም። በሥራ ቦታ ሥልጣን ስላለው ወይንም ስለነበረው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአባልነቱም ይሁን በአመራሩ ከሌላው የበለጠ ሥልጣን ያሰጠዋል ማለት አይደለም። ስም መግለጽ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል እንጂ የአንድ ትልቅ የውጭ ድርጅት የሥራ መሪ በቤተ ክርስቲያን በጽዳት አገልግሎት ይሳተፋል ማለትን ሰምቻለሁ። እውነት ከሆነ በጣም አድንቄዋለሁ። አገልጋይ መሪ እንግዲህ እንደዚህ ያለ ነው ማለት ይቻላል።

እገሌ እኮ ሚኒስትር ነው። ዛሬ ሰበክ፥ ነገ ዘመረ ብንል በእግዚአብሔር ዓይን ከሌላ ሰው የሚለይበት ምንም ነገር የለም። እግዚአብሔር ልብን ያያል፤ ሰው ግን መልክን ያያል። እገሌ እንዲህ ብሎ ሰበኳልና፥ ተናግሯልና ስለዚህ ልክ ነው ማለት አንችልም። መሪ ሆኖ ስለተናገረ ብቻ የእርሱ ንግግር ከሌላው ተራ ሰው የተሻለ መንፈሳዊ ሥልጣን እንዲኖረው አያደርግም። በእርግጥ ሥልጣን በውርስ የሚገኝ መብት ሳይሆን ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ነው። ታማኝነትና ተቀባይነት ማግኘት ግን ሌላ ጉዳይ ነው።

ባለሥልጣንን ማክበር ተገቢና አስፈላጊም ነው። ቢሆንም ባህላችን የጫነብን የበላይን የመፍራትና የመንቀጥቀጥ ሁኔታ አግባብ አይደለም። ኅብረተሰባችን ወደ ላይ የሚመለከት (Vertical Structure of the Society) ሥርዓት ተገዢ ነው። ይህንን በቀላሉ መለወጥ እጅግ አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ ነው መሪዎቻችን ስሕተት ውስጥ የሚገቡትና የበታቹም ሄዶ ችግራቸውን ለመንገር የሚፈራው። ወድቀው ከተነሱ በኋላ ግን ብዙ ብዙ ይላል።

አንድ ጊዜ ኬኔት ፍሌሚንግ የተባለ ሰው «ኅብረተሰቡ አገልጋይ ባሪያን ሳይሆን ሥልጣንን ስለሚያከብር፥ ከማንነትህ ይልቅ ስላለህ ሀብት የሚያከብርህ ይበዛል» ብሎ ነበር። በእኛም አገር ቢሆን የመኪና የፊት መቀመጫ/ጋቢናው ካልተሰጠኝ ብሎ በሚያኮርፍ ሕዝብ መካከል ነው ያለነው።

የማገናዘቢያ ጥያቄ

1. ራእይ ማለት ምንድር ነው? ከሕልምና ከቅዠት በምን ይለያል?
2. የብዙ ጥሎች ዋናው ምክንያት አለመግባባትና አለመደማመጥ ነው ይባላል። ስለዚህ ምን አሳብ አለህ?
3. የሚወክሉ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

የግርጌ ማጣቀሻ (Notes)

1. Alan Loy McGinnis, Bringing out the Best in People, (USA, Lutheran Pub., 1993), P.79.
2. Costas Deir, The Exemplary Leader, (NY, IBS, 1984), P.108.